# አርባዕቱ መጻሕፍተ ብሉያት

## እሉ እሙንቱ

Personal Library of
**Seifu G. Gebreegziabher**
Phone: 972-809-3326

To Abba Yemanebirh

- ❖ መጽሐፈ ጦቢት
- ❖ መጽሐፈ ዮዲት
- ❖ መጽሐፈ አስቴር
- ❖ መጽሐፈ ኢዮብ

አሳታሚ፦ ትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፲፱፻፺፰ ዓ.ም.
አዲስ አበባ።

ያለ ድርጅቱ ፈቃድ መልሶ
ማሳተም ክልክል ነው።

Personal Library of
Seifu G. Gebreegziabher
Phone: 972-809-3326

## ማውጫ



| | ገጽ |
|---|---|
| 1. መጽሐፈ ጦቢት | 1 - 56 |
| 2. መጽሐፈ ዮዲት | 1 - 80 |
| 3. መጽሐፈ አስቴር | 1 - 58 |
| 4. መጽሐፈ ኢዮብ | 1 - 170 |



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

## መግቢያ :

« ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጸ ዚአነ ተጽሕፈ»

የተጻፈው ሁሉ እኛ ልንመከርበት ተጻፈ /ሮሜ ፲፭ : ፬/

እግዚአብሔር አምላክ ለወዳጆቹ ነቢያት፣ ለደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት አዝዞ ያጻፋቸውና ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን የተቀበሉዋቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ቍጥር ፹፩ መሆኑ ፍትሕ መንፈሳዊ በተሰኘው ሕገ - መጽሐፍ ተደንግጎአል።/አንቀጽ ፪/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ልዑል እግዚ አብሔር «እንዲህ ብለህ ተናገር ፣ እንዲህ ብለህ ጻፍ » እያለ ድምጹን ፡ በማሰማት በራዕይ እየገለጸ ፣ በልቡና እየቀረጸ እንዲጻፉ በማ ድረጉ «መጻሕ ፍት አምላካውያት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ነዮን» ቅዱ ሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ናቸው የሚለውን ኃይለ ቃል ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያም ያጠናክራል ። ሃይ/አበ ፸፰ ፥ ፷፯/።

አገራችን ኢትዮጵያ መጻሕፍተ ብሉያትን ከምንጫቸው መቀበሏ በታሪክ ሲወሳ፣ ሲነገርም ይኖራል ። በተግባርም ተተርጉሞአል። «ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» ተብሎ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት የተሰጠላት እናት አገራችን በብሉይ ኪዳን ሕገ ኦሪት፣ በሐዲስ ኪዳን ሕገ ወንጌል ተሰብኮላታል ። ለትምህርት፣ ለሥርዓት፣ ለታሪክና ለሕግ ምንጭ የሆኗት የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት፣ ኑፋቄ በዓለም ላይ ከመዘራቱ አስቀድሞ የገቡላትና የተቀበለቻቸው በመሆኑ ትምህርቷም ሆነ እምነቷ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የጸና ነው።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ ብሔ ራዊት፣ ታሪካዊትና ሐዋርያዊት እንደመሆኗ መጠን ጥንታውያን የሆኑ ጥበባትና ልዩ ልዩ የትምህርት ዓይነቶች አሏት ፣ ከእነዚህም ውስጥ ሊቃውንቱን አራት ዓይና የሚያሰኙአቸው የቅዱሳት መጻሕፍት የትርጓሜ ስልትና ትምህርት ነው። ሥርአተ ትምህርቱም በአራት ዐበይት ጉባኤያት የተከፈለ ሲሆን አራቱ ጉባኤያት በመባል የሚታወቁትም፡- መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትና መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው።

<u>ከ ዲዩቱ መጻሕፍት ብሉያትም ውስጥ፡-</u>

1. መጽሐፈ ጦቢት
2. መጽሐፈ ዮዲት
3. መጽሐፈ አስቴር
4. መጽሐፈ ኢዮብ የተሰኙት ናቸው ።

ሀ. <u>መጽሐፈ ጦቢት</u> ፡- ጦቢት ዐሥሩ ነገድ በ720 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በተማረኩ ጊዜ የተማረከ ጻድቅ ሰው ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው ታሪክም በስደት ሀገር በነነዌ የተፈጸመ መሆኑ ተገልጧል። ቤተ ክርስቲያናችን በቀኖና ከምትቀበላቸው አርባ ስድስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ መጽሐፈ ጦቢት ነው። መጽሐፈ ጦቢት ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናችን ሲነበብ፣ ሲተረጐምና ሲጠቀስ የኖረ ነው ። ለማስረጃም ያህል በስድስተኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ የነበረው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ «ይኄይስ ምጽዋት እምዘጊቦቱ ለወርቅ . . . ወይብሉ በኵሉ ፍናዊሃ ሃሌ ሉያ ይትባረክ እግዚአብሔር . . .» እያለ በመዝሙረ ድጓው ስለጠቀሰው በያሬዳዊ ዜማም ሆነ በሌላ ተቀንዮ ቤተ ክርስቲያናችን ትጠቀምበታለች። (መጽሐፈ ጦቢት ፲፪. ፰ ÷ ፲፫ ፡ ፲፯ ÷ ፲፰ መጽሐፈ ድጓ)።

ለ. <u>መጽሐፈ ዮዲት</u> ፡-መጽሐፈ ዮዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከምትቀበላቸ ው አርባ ስድስት ቀኖናውያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ነው ። መጽሐፉ ልዑል እግዚአብሔር ዮዲት በተባለችው እስራኤላዊት ሴት አማካኝነት ሕዝቡን ከጠላታቸው ሆሎፎርኒስ እንደታደገ የሚተርክ ሲሆን ፣ታሪኩም በአሶር ገናና መንግሥት ጊዜ የተጻፈ ነው ። መጽሐፈ ዮዲት ከጥንት ጀምሮ ሲነበብና ሲጠቀስ፣ ሲተረጐምም የኖረ መጽሐፍ ነው ። ይሁን እንጂ በዛሬው የዕብራውያን ቅዱስ መጽሐፍ ቀኖና ውስጥ ባለመገኘቱ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቊጥር የሚያወጡት ሲኖሩ በሁለተኛው ቀኖናዊ ደረጃ የሚያስቀምጡትም አሉ። ቤተ ክርስቲያናችን ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በመንፈሰ እግዚአብሔር የተጻፉ መሆናቸውን ስለምታምን መጽሐፈ ዮዲትን በተመሳሳይ ቀኖና ከታሪክ መጻሕፍት ቀጥሎ እንዲቀመጥ ተደርጓል። / ፪ጢሞ ፫ ÷ ፲፮ - ፲፯/።

ሐ. መጽሐፈ አስቴር :- መጽሐፈ አስቴር በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት

ከ 486 - 465 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በፋርስ ሀገር የተፈጸመውን የአይሁድ ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ነው፣ ይሁን እንጂ የዕብራውያኑ መጽሐፈ አስቴር አጭር ወይም ጎደሎ ከመሆኑም በላይ በዕብራውያኑ መጽሐፈ አስቴር አንድ ጊዜም እንኳን ስመ እግዚአብሔር አልተጠቀሰበትም፣ ሙሉ በሆነው በኢትዮጵያው መጽሐፈ አስቴር ግን ከሃያ አንድ ጊዜ በላይ ስመ እግዚአብሔር ተጠቅሶ ይገኛል። ምክንያቱም ጸሎተ መርዶክዮስንና ጸሎተ አስቴርን አካትቶ የያዘ በመሆኑ ነው ። /ምዕ ፬ ÷ ፲፯ - ፳፯/።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበለው መጽሐፈ አስቴር ግን በይዘቱ ሙሉ ነው ። ከዕርዐ መጽሐፈ አስቴርም ጋር አንድ አይነት ነው ። በመሆ ኑም ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፈ አስቴርን አንድ ሙሉ መጽሐፍ አድርጋ እንጂ ተጨማሪ ወይም ተረፍ በማለት ከሁለት አትከፍለውም።

መ. መጽሐፈ ኢዮብ :- መጽሐፈ ኢዮብ ከብሉይ ኪዳን ቀደምት መጻሕፍት አንዱ እንደሆነና ጻድቁ ኢዮብ ከነኖረበት ዘመን አንጻር ሊታወቅ ተችሏል ። ጻድቁ ኢዮብ በትውልዱ ከአብርሃም አምስተኛ ትውልድ እንደነበር በምዕራፍ ፴፪ ÷ ፲፮ እስከ ፳ ላይ ተወስቷል ። ጻድቁ ኢዮብ የኖረበት ዘመን ዘመነ አበው ሲሆን መጽሐፉም የተጻፈው በዚሁ ዘመን እንደሆነ ይታመናል ። ሀገረ እግዚብሔር የሆነችው ኢትዮጵያ በቅድሚያ ከተቀበለቻቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ መጽሐፈ ኢዮብ ነው።

ይሁን እንጂ የመጻሕፍተ ብሉያት ምሥጢራዊ ትርጓሜ በግእዝና በአማርኛ በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ተመርሖ ልቡና ተተርጉሞ ቃል በቃልና በእጅ ጽሑፍ ተጠብቆ እስከ እኛ ቆይቷል ። ዛሬ ግን የመጻሕፍቱ ፣ ማለትም የብሉያቱ ምሥጢራዊ ትርጓሜ የእጅ ጽሑፍ የታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም የብሉያት መጻሕፍት ሊቅ የነበሩት መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ ያስተምሩበት የነበረው የብሉያት ትርጓሜ በቀደም ተከተል በማሳተሚያ ድርጅታችን አማካኝነት

ታትሞ ለመምህራንና ለደቀ መዛሙርት እንዲሁም ለሁሉም መፍቀርያነ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲዳረስ ለማድረግ በመቻላችን የታሰበውን የሚያስጀምር ፣ የተጀመረውን የሚያስጨርስ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

«ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት
ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ»

አባ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ
ተክለ ሃይማኖት
፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ሣራንም ለጦብያ ይሰጣት
ዘንድ፤ ወበይእቲ ዕለት ተዘከረ
ጦቢት በእንተ ብሩር ዘአማ
ኅፀነ በኀበ ገባኤል፣ በዚያች
ዕለት ከገባኤል ዘንድ ያኖረ
ውን የብሩን ነገር አሰበ፤
እኔስ ልሙት ብዬ ለመንሁ፤
ልጄን ጦብያን ጠርቼ ሳልሞት
የብሩን ነገር ለምን አልነግ
ረው ልጄ በሞትሁ ጊዜ አክብ
ረህ ቅበረኝ፤ እናትህንም አክብ
ራት፤ በሞተች ጊዜ ከኔ
ደርባት፤ ዑቅ ርእሰከ አወልድየ
እምኵሉ ዝሙት፣ ልጄ
ከዝሙት ራስህን ጠብቅ፤
ወቅድም ለከ ነሚአ ብእሲት
እምዘርዐ አበዊከ፤ አስቀድ
መህ ካባቶችህ ወገን ሚስት
አግባ፤ ከባዕድ ወገን አታግባ፤
እኛ የደጎች ሰዎች ወገኖች
ነንና፤ ወይእዜኒ እነግረከ
በእንተ መካልየ ብሩር ዐሥርቱ
ዘአዕቀብኩ ኀበ ገባኤል፣ ከገባ
ኤል ዘንድ አደራ ያኖርሁት
የብሩን ነገር አሁንም እነግር
ሃለሁ፤ ወአውሥአ ጦብያ
ወይቤሎ እገብር አባ ዘአዘ
ዝከኒ፣ ጦብያ መልሶ እንዲህ
አለው፤ አባቴ ያዘዝከኝን ሁሉ
አደርጋለሁ፤ ወባሕቱ እፎ
እክል ነሚኦቶ ለውእቱ ብሩር
ዘኢየአምሮ፣ ሀገሩን ኣላውቅ
ሰውን አላውቅ ብሩን ለማግም
ጣት እንደምን ይቻለኛል?
ወወሀቦ መጽሐፈ፣ ጠማር
/ደብዳቤ/ ጽፎ ሰጠው፤ አብሮህ
የሚሄድ ሰው ፈልግ፤ ደመወ
ዙን እሰጠዋለሁ አለው፤ ወሖረ
ይኅሥሥ ወረከቦ ለሩፋኤል፣
ሰው ሊፈልግ ሄዶ ሩፋኤልን
አገኘው፤ መልአክ እንደሆነ
አላወቀም፤ ወይቤሎ ትክልኑ
ሐዊረ ምስሌየ ራጊስ ዘሜዶን፣
የሜዶን አውራጃ ወደምትሆን
ወደ ራጊስ ከኔ ጋራ አብሮ
ለመሄድ ትችላለህ? አለው፤
ወይቤሎ ውእቱ መልአክ
እሐውር ምስሌከ፣ መልአኩም
ይሁን ካንተ ጋራ አብሬህ እሄዳ
ለሁ፤ ጐዳናውንም አውቀዋለሁ፤
ከገባኤል ዘንድ ነበርኩ፤ አለው፤
ጦብያም ላባቴ እነግረው ዘንድ
ቆየኝ አለው፤ እሱም ሂድ አትዘ
ግይ አለው፤ ወይቤሎ ለአቡሁ
ነዋ ረከብኩ ዘየሐውር ምስሌየ፤
አባቴን እነሆ ከኔ ጋራ አብሮኝ
የሚሄድ ሰው አገኘሁ አለው፤
ከማን ወገን እንደሆነ አውቅ
ዘንድ ጠርተህ አምጣው አለው፤
ጠርቶ አመጣው፤ ወይቤሎ
ጦቢት አንተ እኁየ እምአይ
ሕዝብ፤ ጦቢትም አንተ ወንድሜ
ከማን ወገን ነህ? ሀገርህስ
ወዴት ነው አለው፤ መልአኩም
ከደመወዜ እንጂ ከሀገሬ፤ ከወገኔ
ምን አለህ አለው፤ ወይቤሎ

ለአቡከ፣ ያባትህ ዓይኖች እንዲገለጡ አውቃለሁ፤ አንተ ግን ዓይኑን ኳለው፣ ወሶበ ተኮሕለ የሐሲ፤ በተኳለ ጊዜ ዓኑን ያሸዋል፣ ብልዙ፣ ብግሩ ይቀረፋል፤ ይገፈፋል አለው፤ ሐና ሔዳ ልጅህ መጣ አለችው፤ ጦቢት ሲወጣ ተሰናክሎ ወደቀ፤ ጡቢያ ፈጥኖ ሄዶ፤ አንገቱን ቀና አድርጎ ኳለው፤ በኳለው ጊዜ ዓይኑን አሸው፣ ብልዙ፣ ብግሩ ተቀረፈለት፤ ተገፈፈለት የልጁን አንገት አቅፎ አለቀሰ፤ ከዚህ በኋላ ጦቢት ጡቢያን ጠርቶ ርኢሎቱ ወልድየ፣ ልጄ የዚያን ሰው ደመወዙን እወቅለት አለው፤ ጡቢያም እኔ ካመጣሁት ገንዘብ እኩሌታውን ቢወስደው አይጐዳም አለው፤ መልአኩንም ጠርቶ ካመጣችሁት ገንዘብ እኩሌታውን ውሰድ አለው፤ ወጸውዖሙ ሩፋኤል ለክልኤሆሙ ሁለቱንም ጠርቶ እንዲህ አላቸው እግዚአብሔርን አመስግኑት፣ ለሱ ተገዙ ስሙን አመስግኑት፤ ወንግሩ ግብሮ፣ ሥራውን በክብር ተናገሩ፤ ወአርእዩ፣ ሥራውን አክብራችሁ ግለጡ፣ ወናሁ ኢዮንብአ እምኔክሙ ኵሎ ነገረ፣ ነገሩን ሁሉ ከናንተ አልሰውረውም፤ ወእቤ ለክሙ ከመ ምሥጢረ መንግሥት ሠናይ ለኃቢዕ፤ የቤተ መንግሥትን ምሥጢር መሠወር ደግ እንደሆነ፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ግን አክብሮ መግለጽ እንዲገባ እነግራችኋለሁ፤ ወይእዜኒ አመ ጸለይክሙ አንተ ወሣራ መርዓትከ አነ አባእኩ ተዝካረ ስእለትክሙ፣ አሁንም ሣራና አንተ በለመናችሁ ጊዜ የልመናችሁን መታሰቢያ ወደ ጌታ አቀረብሁ፤ ወአንተኒ አመ ትቀብር አብድ ንተ፣ አንተም ሬሳ ትቀብር በነበረ ጊዜ በረድኤት አብሬህ ነበርሁ፤ ወእግዚአብሔር ፈነወኒ ከመ እፈውስከ፣ አድንህ ዘንድ እግዚአብሔር ላከኝ፤ ወለሣራኒ ከመ እናገዝ ኃዘና፣ የሣራንም ኃዘኗን አርቅላት ዘንድ ሰደደኝ፤ አነ ውእቱ ሩፋኤል መልአክ አሐዱ እም ፯ቱ ቅዱሳን መላእክት፣ ከ፯ቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ሩፋኤል እኔ ነኝ፤ ወሰሚዖሙ ዘንተ ክልኤሆሙ ወድቁ በገጾሙ ሁለቱም ይህን በሰሙ ጊዜ በግምባራቸው ፍግም ብለው ወደቁ፤ ወይቤሎሙ ኢትፍርሁ፣ አትፍሩ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ እስመ አኮ ሊተ አኩቴት፣ ለኔ ምስጋና የሚገባኝ አይደለምና፤ አላ

ፈቃዶ ለአምላክከሙ አምጽ አኒ። የፈጣሪያችሁ ፈቃዱ አመጣኝ እንጂ፤ ወአንሰ አስተር አይኩ ክሙ፤ እኔ ታየኋችሁ እናንተም መልኬን አያችሁት፤ ከናንተ ጋራ ይረባኛል፤ ይጠቅ መኛል ብዬ አልበላሁም፤ አልጠ ጣሁም፤ ወይእዜኒ እመኑ በእግ ዚአብሔር፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ እኔ ወደላከኝ እሄዳ ለሁና፤ ወመጻእኩ እጽሐፍ እሉንተ ኵሉ፤ ይህን ሁሉ እጽፍ ዘንድ መጣሁ፤ ወሶቤሃ ተንሥአ ወሖረ፤ ያን ጊዜ ተነሥቶ ሄደ፤ ወኢርእይዎ እንከ፤ ዳግመኛ አላዩትም፤ ወበእንተ ዘአስተር አዮሙ መልአከ እግዚአብሔር፤ መልአከ እግዚአብሔር ስለታ ያቸው፤ ወጸለየ ጦቢት ጸሎተ ትፍሥሕት ተናገረ ሲል ነው፤ ጦቢትም ደስ የሚያሰኝ ጸሎት ተናገረ፤ ወይቤ ይትባረክ እግዚ አብሔር ዘውእቱ ሕያው ለዓለም፤ ለዘለዓለሙ ሕያው ሆኖ የሚኖር እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን እያለ ብዙ ምስጋና ተናገረ፤ ወእምዝ አርመመ ጦቢት እምነበ ይጼሊ፤ ከዚህ በኋላ ጦቢት ጸሎቱን ተወ፤ ፶ወ፰ቱ ዓመት ሎቱ አመ የኃጕል አዕይንቲሁ፤ ዓይኑም በጠፋ ጊዜ ሃምሳ

ስምንት ዘመን ሁኖት ነበረ፤ ወእምድኅረ ፶ወ፰ቱ ዓመት ርእየ ከኃምሳ ስምንት ዘመን በኋላ አየ፤ ወገብረ ምጽዋተ፤ ምጽዋቱን መጸወተ፤ ወወሰከ ዓዲ ፈሪሆቶ ለእግዚአብሔር፤ ዳግመኛ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ፈራው፤ ወይእዜኒ ጻእ ወልድየ እምነ ነነዌ እስመ በግብር ይከውን ዘነበበ ዮናስ ነቢይ፤ ዮናስ የተናገረው ነገር አይቀር ምና ልጄ ከነነዌ ውጣ፤ ወአንተ ዕቀብ ሕገ ወትእዛዘ፤ አንተም ሕጉን ትእዛዙን ጠብቅ፤ ወቅብ ረኒ በሠናይ፤ አክብረህ ቅበረኝ እናትህንም ከኔ ደርባት፤ ወይእ ዜኒ ወልድየ ርኢ ከመ ታድኅን ምጽዋት፤ አሁንም ልጄ ምጽ ዋት ለሚያደርጓት ሰዎች ከሞተ ሥጋ፤ ከሞተ ነፍስ እንድታ ድን እወቅ፤ ወከመዝ ብሂሎ ሞተ ጦቢት፤ ጦቢት ይህንን ተናግሮ ሞተ፤ ወወጽአት መን ፈሱ፤ ነፍሱ ከሥጋው ተለየች፤ ምእት ወሃምሳ ወስመንቱ ዓመት ሎቱ፤ በሞተ ጊዜ መቶ ሃምሳ ስምንት ዘመን ሁኖት ነበር፤ ወቀበርዎ በክብር፤ አክብረው ቀበሩት፤ እናቱ ሐናም በሞተች ጊዜ ጦብያ ካባቱ ደረባት፤ ከዚህ በኋላ ጦብያ ልጆቹን ሚስቱን ይዞ ከራጉኤል ዘንድ ወደባጥና ሄደ፤ ራጉኤልም፤

እድናም ሞቱ ቀበራቸው፤ ወሰምዐ ናቡከደነፆር ወአሕሻዊሮስ ሙስናሃ ለነነዌ ወተፈሥሐ፤ ናቡከደነፆርና አሕሻዊሮስ የነነዌን ጥፋት ሰምተው ደስ አላቸው፤ ወሞተ ጦብያ በ፻ወ፳ወ፯ ዓመት፤ ጦብያም በመቶ ሃያ ሰባት ዓመቱ ሞተ፤ አክብረው ቀበሩት ይህም ተጻፈ፤ ተጽፎ ሲነበብ፣ ሲተረጐም ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ደረሰ፤ ሐዋርያት ለቀሌምንጦስ ሰማንያ አንዱን መጻሕፍት ቈጥረው ሲሰጡት አንድ መጽሐፈ ጦቢት ብለው ቆጥረው ሰጥተውታል፤ ይኸም ለከንቱ አልተጻፈም፣ እኛ ልንገሥጽበት፣ እኛ ልንመከርበት ነው፤ ወኮሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጸ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክ ሎተ መጽሐፍ ንርከብ ተስፋነ እንዲል፤ ይህ አርእስት ነው፤ ሠለስቱ ምእት ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፤ ነገሩን መጽሐፈ ነገሩ ለጦቢት ብሎ ያመጣል።

## ምዕራፍ ፩

፩፡ መጽሐፈ ነገሩ ለጦብያ ወልደ ጦቢት፤

መጽሐፈ ነገሩ ለጦቢት አበ ጦብያ ሲል ነው፤ የጦብያ አባት ጦቢት የተናገረው ነገር ይህ ነው፤ አንድም እንዳለበት ይሆናል፤ የጦቢት ልጅ ጦብያ የተናገረው ነገር ይህ ነው፤ በውስጡ የሱ ነገር አለበትና፤

ወልደ ገባኤል፤

ጦቢትን የገባኤል ልጅ አለው፤

ዘእምነ አሳሔል፤

ገባኤልን ከአሳሔል የተወለደ፤

ዘእምነገደ ንፍታሌም፤

አሳሔልን ከነገደ ንፍታሌም የተወለደ አለው፤

፪፡ ዘተጼወወ በመዋዕለ አኔሜሴር ንጉሠ ፋርስ፤

በፋርስ ንጉሥ በአኔሜሴር ዘመን የተማረከ፤

ዘእምታቢስ እንተ እምየማና ለቃዴስ፤

የቃዴስ ቀኝ ከምትሆን ከታቢስ የተማረከ፤

ዘእንተ ንፍታሌም ዘገሊላ፤

የገሊላ ክፋይ ከምትሆን ከንፍታሌም ዕጣ የተማረከ፤

እንተ መልዕልተ አሴር፤

ገሊላን ከነገደ አሴር ዕጣ በላይ ያለች አላት፤

፫፡ አነ ጦቢት በፍኖተ ጽድቅ ሖርኩ፤

እኔ ጦቢት በእውነተኛ ሕግ ጸንቼ ኖርሁ፤

ወበርትዕ ሖየውኩ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ፤

ባለ በዘመኔ ሁሉ በቀና ሕግ ጸንቼ ኖርሁ፤ ምንው ይኸግ ትምክህት አይሆንበትም ቢሉ አይሆንበትም፤ አብነት ለመሆን ነው፤ ዕቀባ ለነፍስየ እስመ የዋህ አነ እንዳለው ያለ ነው፤

ወምጽዋትየኒ ብዙኃ ገበርኩ ለአኃውየ ወለሕዝብየኒ እለ ሖሩ ምስሌየ ብሔረ ፋርስ ውስተ ነነዌ፤

በፋርስ ወዳለች ወደ ነነዌ ከኔ ጋራ ለሄዱ ለወገኖቼ፤ ለወንድሞቼ ብዙ ምጽዋትን ሰጠሁ፤

፬፡ ወእንዘ ሀሎኩ ምስለ ደቂቀ እስራኤል በብሔርየ እንዘ ንዑስ አነ፤

እኔ ሕፃን ሳለሁ በሀገሬ ከእስራ ኤል ልጆች ጋራ ሳለሁ፤

ወኵሉ ሕዝበ ንፍታሌም ወአቡየ ክህዱ፤

የንፍታሌም ወገኖች አባቴን በደሉ፤

እምነ ኢየሩሳሌም እንተ ኃረይዋ እምነ ኵሉ እስራኤል፤

እስራኤል ከሀገሩ ሁሉ ከመረ ጧት ከኢየሩሳሌም ሥርዓት ወጥተው በደሉ፤

ከመ ይሡዑ ውስቴታ ኵሉ እስራ ኤል፤

እስራኤል ይሠውባት ዘንድ ከመረጧት ወጥተው፤

ወተቀደሰ ጽርሐ መቅደሱ ለልዑል፤

ወእምዘ ተቀደሰ ሲል ነው፤ የልዑል የእግዚአብሔር ማደ ሪያ ከምትሆን ከነበረች ከቤተ መቅደስ ሥርዐት ወጥተው በደሉ፤

ወተሐንፀ ሎሙ ለትውልድ ዘለዓለም፤

ለዘለዓለሙ ለልጅ ልጅ ሊሆን ከተሠራላቸው ከቤተ መቅደስ ሥርዓት ወጥተው በደሉ፤

፭፡ ወኵሉ ሕዝብ እለ ክህዱ ሦዑ ለበዓል፤

ከሕጉ ከሥርዓቱ የወጡ ሕዝቡም ለጣዖት ሠዉ፤

ወለደማሊ፤

ለአንበሳ ምስል ሠዉ፤

ወቤተ ንፍታሌምኒ፤

የንፍታሌም ወገኖች፤

ወቤተ አቡየ ኀብሩ ምስሌሆሙ፤

የንፍታሌም ወገኖችና የአባቴ ወገኖች ከነዚያ ጋራ ተባበሩ፤

፮፡ ወአነ ባሕቲትየ መብዝኅቶ አሐውር ኢየሩሳሌም አመ በዓላት፤

በበዓለ መጸለት፣ በበዓለ ሠዊት፣ እኔ ብቻዬን ብዙ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም እሄድ ነበር፤

፲፩፤ ወአንሰ ዓቀብኩ ነፍስየ ከመ ኢይብላዕ፣

እኔ ግን ተረፈ መሥዋቱዕቱ ጣዖቱን እንዳልበላ ሰውነቴን ጠበቅሁ፤

፲፪፤ እስመ እዜከሮ ለእግዚአብሔር በኵሉ ልብየ፣

በፍጹም ልቡናዬ እግዚአብ ሔርን አስቤዋለሁና፤

፲፫፤ ወወሀበኒ እግዚአብሔር ገጸ ወሞገሰ በቅድመ አኔሜሴር፣

እግዚአብሔርም በአኔሜሴር ፊትፍጹም ባለሟልነትን ሰጠኝ፤

ወሢመኒ መጋቤሁ፣

በወገኖች ላይ ሾመኝ፤

፲፬፤ ወሖርኩ ምድየም፣

ወደ ምድያም ሄድሁ፤

ወአዕቀብክዎ ለገባኤል በብሔረ ራጊስ ዘምድያም ፲ተ መካልየ ብሩር፣

በምድያም አውራጃ በምትሆን በራጊስ ዐሥር መክሊት ብር ለገባኤል አደራ ሰጠሁት፤

፲፭፤ ወአመ ሞተ አኔሜሴር ነግሠ ህየንቴሁ ሰናክሬም ዘእኩይ ምግባሩ፣

አኔሜሴር በሞተ ጊዜ ስለርሱ ፈንታ ግብሩ ክፉ የሆነ ሰናክሬም ነገሠ፤

ወሠዐረኒ፣

ከሹመቴ ሻረኝ፤

ወኢክህልኩ ሐዊረ ምድየም፣

ወደ ምድያም መሄድ አልተቻ ለኝም፤

፲፮፤ ወበመዋዕለ አኔሜሴር ብዙኃ ምጽዋተ ገበርኩ ለአኃውየ፤

በአኔሜሴርም ዘመን ለወንድ ሞቼ ብዙ ምጽዋት ሰጠሁ፤

፲፯፤ ወእክልየኒ ወሀብኩ ለርኁባን፣

እህሌንም ለተራብ ሰዎች ሰጠሁ፤

ወልብስየኒ ለዕሩቃን፣

ልብሴንም ለተራቆቱ ሰዎች ሰጠሁ፤

ወእመቦ ዘርኢኩ እምሕዝብየ ምውተ ግዱፈ ኀበ ዓረፍት በነነዌ እቀብሮ፣

ከወገኖቼ ሙቶ ካደባባይ የወደቀ ሰው ያየሁት ቢኖር በነነዌ እቀብረው ነበረ፤ ይህ የቀደመ ግብሩ ነው፤

፲፰፤ እመቦ ዘቀተለ ሰናክሬም ንጉሥ አመ አተወ እምይሁዳ እንዘ ይጐይይ፣

ሰናክሬም ሸሽቶ ከይሁዳ በተመለሰ ጊዜ የገደለው ሰው ቢኖር፤

ወአነ ቀበርክዎሙ ጽሚተ፣

ተሰውሬ እቀብራቸው ነበር፤

እስመ ብዙኃነ ቀተለ በመዓቱ፣

እሱ የኔን ወገን ቢያጠፋ እኔ የእሱን ወገን አላጠፋም? ብሎ ተቆጥቶ ብዙ ሰው አጥፍቷልና፤

ወ፡ነሥሡ ንጉሥ አብድንቲሆሙ ወኢረከቦሙ፣

ንጉሥ ሬሳቸውን ፈለገ፤ አላገኛ ቸውም፤

፲፱፤ ወሖረ አሐዱ እምሰብአ ነነዌ ኀበ ንጉሥ፣

ከነነዌ አንድ ሰው ከንጉሥ ዘንድ ሄደ፤

ወአስተዋደየኒ ከመ አነ ቀበርክ ዎሙ፣

እኔ እንደቀበርኳቸው ነገሮ አጣላኝ፤

ወተኀባዕኩ ሶበ አእመርኩ ከመ ይፈ ቅዱ ይቅትሉኒ፣

ይገድሉኝ ዘንድ እንደወደዱ ባወቅሁ ጊዜ ተሰወርሁ፤

ወፈሪህየ ተግኀሥኩ፣

ፈርቼ ሸሸሁ፤

፳፤ ወሶበ ኃጥኡኒ በርበሩ ኵሎ ንዋይየ፣

ባጡኝ ጊዜ ገንዘቤን በዘበዙ፤

ወአልቦ ዘአትረፉ ሊተ ዘእንበለ ሐና ብእሲትየ፣

ከሐና በቀር ከገንዘቤ ያስቀሩ ልኝ የለም፤ አንድም አግብአ ሊት ሐናሃ ይላል፤ ሐና ሳትቀር፤

ወጦቢያ ወልድየ፣

ከልጄ ከጦብያ በቀር፤ አንድም ጦብያ ሳይቀር፤

፳፩፤ ወኢወዓእኩ ሃምሳ ወሐምስተ መዋዕለ፣

ሐምሳ አምስት ቀን ከተሠ ወርሁብት አልወጣሁም፤

እስከ አመ ቀተልዎ ክልኤሆሙ ደቂቁ ወጐዩ ውስተ አራራት፣

እስራ ስምንት እልፍ ከአምስት ሽህ ሰው አጥፍቶ መጥቶ በግን ሊነግሥ ነው ብለው ሁለቱ ልጆቹ ገድለውት ወደ አራራት እስኪሄዱ ድረስ አልወጣሁም፤ አራራጥም ይላል፤ ጐዩ ባለው ጐየይኩ ይላል፤

ወነግሠ አስራዶን ወልዱ ህየንቴሁ፣

ልጁ አስራዶን ስለ እርሱ ፋንታ ነገሠ፤ ይህ ከነገር ያልገባ ነው፤ ብዙ ስም አለው፤ ሆነ ሐርድን አስበ ቀፈት ንዑስ ስናክሬም ይለዋል፤

ወሤሞ ለአካኪሮን ወልደ አሳሔል ወልደ እኁየ ላዕለ ኵሉ ቤተ አቡሁ፤

የወንድሜ የአሳሔልን ልጅ አካኪሮስን ባባቱ ወገኖች ላይ ሾመው፤

ወላዕለ ኵሉ ሥርዓቶሙ፣

በሥርዓተ ክህነት ላይ ሾመው፣

፳፪፤ ወሰአሎ በእንቲአየ አካኪሮን፤

አካኪሮን ስለኔ ለመነው፤

ወአዕተወኒ ውስተ ነነዌ፣

ወደ ነነዌ መለሰኝ፤

ወአክኪሮን ዘላዕሌሁ ማኅተም፣

የንጉሥ ማኅተም በእጁ ያለ አካኪሮን፤ አንድም ማሕተተ ይላል፣ ምርኰሪ ያለው፤

ወዓዕዓዓ ቤቱ፣

የቤቱ ገንዘብ ሁሉ በጁ ያለ አካኪሮን፤

ወሤመ ዳግመ አክሮንድስሃ፣

ዳግመኛ አክሮንድስን ሾመ።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወሶበ አተውኩ ቤትየ፣

ብሔርየ ሲል ነው፤ ወደሀገሬ በተመለስሁ ጊዜ፤

አግብኡ ሊተ ሐናሃ ብእሲትየ፣

ሚስቴን ሐናን መለሱልኝ፤ ወጠ ብያሃ ወልድየ ልጄን ጦብያንም መለሱልኝ፤

በዕለተ በዓለ ጳንጠቈስጤ ቅድስት፣

ክብርት የምትሆን በዓለ ጳንጠ ቈስጤን በሚያከብሩባት ቀን፤

ሳብዕ ሰንበት፣

በሰባተኛው ሱባዔ፤

ገብሩ ላዕሌየ ሠናየ፣

ለኔ በጎ ነገር አደረጉልኝ፤

ወረፈቁ እብላዕ፣

እበላ ዘንድ ተቀመጥሁ፤

፪፤ ወርኢኩ ከመ መስየ በሕቁ፣

ፈጽሞ እንደመሸ አይቼ፤

ወእቤሎ ለወልድየ ሑር አምጽእ ዘረከብከ እምአኃዊነ ቢጸ ነዳያን፣

ዕደወ ነዳያን ሲል ነው፣ ችግረኞችን ሰዎች አምጣ፤ አንድም በችጋር የተካከሉ ድኆችን አምጣ አልሁት፣

እለ ተዘከርክዎ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን አስቤዋለሁና፤

እጸንሐከ እስከ ትገብእ፣

እስክትመለስ ድረስ እጠብቅ ሃለሁ አለው፤

፫፤ ወሶበ ገብአ ወይቤለኒ፣

በተመለሰ ጊዜ እንዲህ አለኝ፤

አባ ረከብኩ አሐደ እምሕዝብ፤

አባቴ ከወገኖቻችን አንድ ሰው አገኘሁ፤

ወግዱፍ በድኑ ውስተ ምሥያጥ፣

ሬሳው ባደባባይ ወድቋል አለ፤

፬፤ ወአነሂ ተንሣእኩ ዘእንበለ እጥ ዓም እክለ፣

እኔም እህል ሳልቀምስ ተነሥቼ፤

ወአባዕክዎ ውስተ አሐዱ ቤት እስከ የዓርብ ፀሐይ፣

ፀሐይ እስቲገባ ድረስ ካንዱ ቤት ውስጥ አስገባሁት፤

፭፡ ወገባዕኩ ውስተ ቤትየ።

ወደቤቴ ገባሁ፤

ወተሐፀብኩ ወበላዕኩ እክልየ በኀዘን።

ታጥቤ እያዘንሁ እህሉን በላሁ፤

፮፡ ወተዘከርኩ ዘይቤ አሞጽ ይትመየጥ በዓላቲክሙ ውስተ ላሀ።

አሞጽ በዓለ መጸለት በዓለ ሠዊት ወደኀዘን ይመለሳል ያለውን አሰብሁ፤

ወኵሉ ትፍሥሕትክሙ ውስተ ብካይ።

ደስታችሁ ሁሉ ወደ ለቅሶ ይመለሳል ያለውን አሰብሁ።

፯፡ ወእምዝ በከይኩ።

ከዚህ በኋላ አለቀስሁ፤

ወሶበ ዓርበ ፀሐይ።

ፀሐይ በገባ ጊዜኔ

ሖርኩ ወከረይኩ ወቀበርክዎ።

ሄጄ መቃብር ቆፍሬ ቀበርኩት፤

፰፡ ወሰሐቁ ላዕሌየ ሰብአ ብሔር ወይቤሉ።

በኔ ላይ ሳቁ፣ እንዲህ አሉ፤

ኢይፈርህኑ ዝንቱ ኢይቅትልዎ በእንተ ዝንቱ ግብር።

ስለዚህ ነገር እንዳይገድሉት አይፈራምን፤

እስመ ይቀብሮሙ ለእለ ቀተለ ንጉሥ።

ንጉሥ የገደላቸውን ይቀብራቸዋልና፤

፱፡ ወበይእቲ ሌሊት ቤትኩ ስኩብየ ውስተ ዓረፍተ ዓፀድ።

በዚያች ሌሊት ከቅጽሩ ተኝቼ አደርሁ፤ አንድም ስዑብየ ይላል፤ የተዳደፍሁ ሁኜ አደርሁ፤

ወክሡት ገጽየ።

ፊቴ ተገልጦ ነበረ፤

፲፡ ወኢየእመርኩ ከመ ቦቱ አዕዋፍ ውስተ ዓረፍት።

በቅጽሩ አዕዋፍ እንዳሉ አላወቅሁም ነበር፤

ወእንዘ ክሡት ገጽየ አኰሰሓ እልክቱ አዕዋፍ ውዑየ ውስተ አዕይንትየ።

ፊቴ ተገልጦ ሳለ አዕዋፍ ትኩስ ፋንድያ ባይኔ ላይ ጣሉብኝ፤

ወወጽአኒ ጢስ ውስተ አዕይንትየ።

በዓይኔ ብልዝ ወጣብኝ፤

ወሖርኩ ኀበ ዓቀብተ ሥራይ።

ወደባለ መድኃኒቶች ሄድሁ፤

ወአልቦ ዘበቍዓኒ።

የረባኝ የጠቀመኝ የለም፤

ወአካኪሮስ ይሴስየኒ እስከ አመ ሖርኩ ኤልማድያ ባሕቲትየ።

ብቻዬን ኤልማድያ እስክሄድ ድረስ አካኪሮስ ይመግበኝ ነበረ፤

፲፩፡ ወሐናስ ትፀመድ ቤተ አንስት።

ሐና ግን እመቤቶቿን ታገለግል ነበረ፤

፲፪፡ ወለአከት ኀበ አጋዕዝቲሃ፣

ከጌቶቿ ዘንድ ላከች፤

ወወሀብዋ እማንቱሂ መሐስዓ፤

እነዚያም ደመወዟን አንድ ጠቦት ሰጧት፤

ወአምጽአት ኀቤየ፣

ወደኔ አመጣቻት፤

፲፫፡ ወሶበ መጽአት ኀቤየ፣

ወደኔ በመጣች ጊዜ፤

አኀዘት ትጽራኅ፣

በጊቱ ትጮህ ጀመር፤ አንድም ሐና በግ አመጣሁ እያለች፤

ወእቤላ እምአይቴ ዛቲ መሐስዕ

ይችን ጠቦት ከወዴት አመጣ ሻት አልኋት፤

ወለእመ ሰረቂዮ አግብኢዮ ለባዕሉ እስመ ኢኮነ ጽድቀ በሊዐ ዘሰርቅ፤

የተሰረቀ ገንዘብ መብላት አይገባምና ለባለቤቱ መልሺ አልኋት፤

፲፬፡ ወትቤለኒ ጸገውኒዮ ሀየንተ አስብየ፣

ስለደመወዜ የሰጡኝ ነው አለችኝ፤

ወኢአመንክዋ፣

እኔ ግን አላመንኋትም፤

ወእቤላ አግብኢ ለባዕሉ፣

ለባለገንዘቡ መልሽ አልኋት፤

ወብዙኀ ተኀአዝኩ ምስሌሃ፣

ከሷ ጋራ ብዙ ተከራከርሁ፤

ወአውሥአት ወትቤለኒ፣

መለሰች እንዲህ አለችኝ፤

አይቴ ውእቱ ምጽዋትከ ወጽድቅከ፣

ምጽዋትህ በጎነትህ ወዴት ነው አለችኝ፤

ናሁ ኵሉ ተአውቀ ዘላዕሌከ፣

እነሆ ክፋትህ ሁሉ ተገለጸብህ።

## ምዕራፍ ፫

፩፡ ወተከዝኩ በሕማየ፣

በመከራዬ አዘንሁ፤

ወጸለይኩ ወበከይኩ፣

አልቀሼ ለመንሁ፤

፪፡ ወእቤ ጻድቅ አንተ እግዚኦ፣

አቤቱ አንተ ቸር ነህ አልሁ፤

ወኵሉ ፍናዊከ፣

ሥራህ ሁሉ የቀና ነው፤

በምሕረት ወበፍትሕ፣

በይቅርታ በፍርድ የቀና ነው፤

በርትዕ ወበጽድቅ ትኴንን ዓለመ፣

በእውነት ነገር፣ በቀና ነገር ዓለሙን ሁሉ ትገዛለህ፤

፫፡ ተዘከረኒ ወነጽረኒ፣

እንዲህ የምታደርግ አንተ በቸርነትህ አስበኝ፤ በዓይነ ምሕረት ተመልከተኝ፤

ወኢትትበቀለኒ በኃጢአትየ፣

በኃጢአቴ ተበቅለህ አታጥፋኝ፤

፬፤ ወበኃጢአተ አበውየ እለ አበሱ ለከ ወኢሰምዑ ትእዛዘከ፣

ትእዛዝህን ባልሰሙ አንተን በበደሉ ባባቶቼ ኃጢአት አታጥፋኝ፤

ወረሰይከነ ለተበርብሮ ወለፂዌ ውፃ ወለተቀትሎ፣

ለመበዝበዝ፣ ለመማረክ፣ ለሞት አደረግኸኝ፤

ወኮነ ትዕይርተ ውስተ ኵሉ ዓለም፣

በዓለም ሁሉ መገዳደሪያ ሆነ፤

ወአሕዛብ እለ እምውስቴቶሙ ተዘርውነ ኀቤሆሙ፤

ተማርከን በሄድንበት በዓራቱ መዓዝን ባሉ በአሕዛብ ዘንድ መገዳደሪያ ሆነ፤

፭፤ ወይእዜኒ ርቱዕ ውእቱ ኵነኔከ ዘበጽድቅ፣

አሁንም ሕግህ በእውነት የቀና ነው፣

ወግበር ሊተ በዘይሠረይ ኃጢአትየ ወዘአበውየ፤

የኔም የአባቶቼም ኃጢአት በሚሠረይ ገንዘብ እንዲሠረይ አድርግልኝ፤

እስመ ኢገበርነ ትእዛዘከ፤

ትእዛዝህን አልፈጸምንምና ምንም ባንፈጽም፣

ወኢሖርነ በጽድቅ ቅድሜከ፣

በፊትህ በእውነተኛው ሕግ ፀንተን አልኖርንምና ምንም ባንኖር፤

፮፤ ወይእዜኒ ዘይኤድመከ ግበር ምስሌየ በቅድሜከ፣

አሁንም በፊትህ ደስ የሚያሰኝህን ነገር አድርግልኝ፤

ወአዝዝ ዘይትሜጦ መንፈስየ ከመ እሠዓር፤

ከዚህ ዓለም በሞት እለይ ዘንድ ነፍሴን ከሥጋዬ የሚለይ መልአክ እዘዝ፣

ወእኩን መሬተ፣

ትቢያ እሆን ዘንድ፤

እስመ ይኄይሰኒ መዊት እምነቢሮ፣

ክፉ ነገር እየሰሙ ከመኖር ሞት ይሻላልና፣

እስመ ሰማዕኩ ትዕይርተ በሐሰት፣

በሐሰት ተግዳሮትን ሰምቻለሁና፤

ወበዝኀ ኃዘን ላዕሌየ፤

ኃዘን በኔ ላይ በዝቷልና፣

ወአዝዝ እሠዐር እምሕማምየ ውስተ መካን ዘለዓለም፤

በመንግሥተ ሰማይ ለመኖር ከኃዘን ከመከራ እለይ ዘንድ እዘዝ፤

ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ፤

ገጸ ረድኤትህን ከኔ አትመልስ፤

## ጉባዔ

፯፡ ወበይእቲ ዕለት ረከባ ለወለተ ራጉኤል ሣራ እምነ መጣኒ ዘሜዶን፣

የሜዶን አውራጃ በምትሆን በመጣኒ የራጉኤል ልጅ የምት ሆን ሣራን በዚች ቀን ተግዳ ሮት አገኛት፤

ወተአየራሃ አዕማተ አቡሃ፣

ያባቷ ባሮች ተገዳደሯት፣

፰፡ እስመ አስተዋስብዋ ለሰብዓቱ ዕደው፣

ለሰባት ሰዎች አጋብ ተዋት ነበርና፤

ወቀተሎሙ ጋኔን እኩይ አስማንድ ዮስ ዘእንበለ ይቅረብዋ እንተ ብእሲ ወብእሲት፣

በሴትና በወንድ ልማድ ሳይቀ ርቧት አስማንድዮስ የሚባል ክፉ ጋኔን ገድሏቸዋልና፤

ወይቤላሃ ኢተአምሪኑ እንዘ ይትሐነቁ ዓምታትኪ፣

ባሎችሽ እየታነቁ እንደሞቱ አታውቂምን አሏት፤

ወናሁ ሰብዓቱ አውሰቡኪ፣

እነሆ ሰባት ሰዎች አግብተውሽ ነበረ፤

ወአሐዱ እምኔሆሙ ኢተለወኪ፣

ከነዚያ አንዱ በግብር በቦታ አል ተከተለሽም፤ አንድም አልደ ረሰብሽም፤ አንድም ኢተለወኪ ቢል በግብር በቦታ አላወቅ ሽውም፤

፱፡ ወምንተ እንከ ተቀሥፍነ በእንቲ አሆሙ፣

በነዚያ ምክንያት ምን ያህል ያዝን መስሎሻል፤

እስመ ሞቱ ሐሩ ምስሌሆሙ፤

እነዚያም ሙተዋልና አንቺም እደነዚያ በሞት ሂጂ፤

ወኢንርአይ ወልደ ወወለተ እምኔኪ ለዓለም፣

ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ ካንቺ ተወለደ ማለት ለዘለዓለሙ ይቅርብን፤

፲፡ ወሶበ ሰምዐት ዘንተ ተከዘት ጥቀ፣

ይህን ሰምታ እጅግ አዘነች፤

እስከ ትፈቅድ ትትሐነቅ፣

ትታነቅ ዘንድ እስክ ትወድ ድረስ፤

ወትቤ አሐቲ አነ ለአቡየ፤

እኔ ላባቴ አንዲት ነኝ፤

ወእመ ገበርኩ ዘንተ ከመዝ ትዕይርተ እከውኖ፤

እንዲህ ያለ ነገር ባደርግ ተግዳሮት እሆነዋለሁ፤ አንዲት ልጅ ነበረችው ታንቃ ሞተች ተብሎ፤

ወአወርድ ርስዓኒሁ በፃዕር ውስተ መቃብር፣

ያረጀ ሰውነቱን በፃዕር በመከራ ሳለ ወደመቃብር አወርደዋለሁ፤

፲፭፤ ወጸለየት በውስተ ቤታ።

በቤቷ ውስጥ ትጸልይ ጀመረች፤

ወትቤ ቡሩክ አንተ እግዚኦ አምላኪየ።

ፈጣሪዬ አቤቱ አንተ ክቡር ምስጉን ነህ፤

ወይትባረክ ስምከ ቅዱስ።

ክቡር የሚሆን ስምህ ይክበር፤ ይመስገን፤

ወቡሩክ ስምከ በኵሉ ዓለም።

በዓለም ሁሉ ስምህ ክቡር፤ ምስጉን ነው፤

ወክቡር ኵሉ ግብርከ ለዓለም፤

ሥራህም ለዘለዓለሙ ክቡር ነው፤

፲፮፤ ወይእዜኒ እግዚኦ አዕይንትየ ወገጽየ ለከ መጠውኩ።

ዓይኔ ልቡናዬን፤ ገጽ ልቡናዬን አቤቱ ወዳንተ መለስሁ፤

፲፯፤ ወእብለከ ሠዓሪኒ እምነ ምድር ከመ ኢይስማዕ ትዕይርተ፤

ተግዳሮትን እንዳልሰማ ከዚህ ዓለም በሞት ለዩኝ፤

፲፰፤ ለሊከ እግዚኦ ተአምር ከመ ንጽሕት አነ እምኵሉ ኃጢአት ዘምስለ ብእሲ።

ከወንድ ጋር ከሚያደርጉት ኃጢአት እኔ ንጽሕት እንደሆንሁ አቤቱ አንተ ታውቃለህ፤

፲፱፤ ወኢያገመንኩ ስምየ ወስመ አቡየ በብሔር ዘተፄወውኩ።

ተማርኬ በሄድሁበት ሀገር የኔንም ያባቴንም ስም አላስነቀፍሁም፤

ወአሐቲ አነ ለአቡየ።

እኔ ላባቴ አንዲት ነኝ፤

ወአልብየ እኁ።

እኔ ወንድም የለኝም፤

ወአልብየ ዘቅሩብ።

አቅራቢያ ዘመድም የለኝም፤

ወእትዓቀብ ለብእሲ እስመ ሰብዓቱ ሞቱኒ።

ሰባቱ ባሎቼ ሙተውብኛልና ለስምንተኛው እጠብቃለሁ፤

ለምንት እንከ አሐዩ።

እንዲህ እየሆንሁ ለምን እኖራለሁ፤

ወለእመኒ ኢፈቀድከ ትቅትለኒ ነጽር ላዕሌየ።

ትገድለኝ ዘንድ ካልወደድህ በዓይነ ምሕረት ተመልከተኝ፤

ወእስተምሕረኒ።

እዘንልኝ፤

ወአዝዝ ከመ ኢይስማዕ ትዕይርተ እንከ።

ከእንግዲህ ወዲህ ተግዳሮት እንዳልሰማ እዘዝ፤

፲፮፡ ወተሰምዓ ጸሎቶሙ ለክልኤሆሙ በቅድመ ስብሐተ ዕበዩ ለእግዚአብሔር፣

በእግዚአብሔር በገናንነቱ፣ በጌትነቱ ፊት የሁለቱ ልመና ቸው ተሰማ፤

፲፯፡ ወፈነዎ ለሩፋኤል ከመ ይፈውሶሙ ለክልኤሆሙ፣

ሁለቱንም ያድናቸው ዘንድ ሩፋኤልን ላከው፤

ወለጦቢትኒ ከመ ያሰስል ጢሰ ዓይኑ፣

ጦቢትንም የዓይኑን ብልዝ ብግር ያጠፋለት ዘንድ፤

ወለሣራኒ ወለተ ራጉኤል ከመ የሀባ ለጦብያ ወልደ ጦቢት ትኩኖ ብእሲቶ፣

የራጉኤል ልጅ ሣራን ሚስት ትሆነው ዘንድ ለጦቢት ልጅ ለጦቢያ ይሰጣት ዘንድ፤

ወከመ ይሥዓሮ ለአስማንድዮስ ጋኔን እኩይ፣

ክፉ ጋኔን አስማንድዮስንም ያጠፋው ዘንድ፤

እስመ ጦብያ ይወርሳ፣

ጦቢያ ያገባታልና፤

ወበእማንቱ መዋዕል ተመይጠ ጦቢት ወቦተወ ቤቶ፣

ወሖርኩ ኤልማድያ ብሎ ነበርና በዚያ ወራት ጦቢት ተመልሶ ከቤቱ ገባ፤

ወሣራኒ ወለተ ራጉኤል ወረደት እምነ ጽርሐ ላዕላይ፣

የራጉኤል ልጅ ሣራም ከሰገነቱ ወረደች።

## ምዕራፍ ፬

፩፡ ወበይእቲ ዕለት ተዘከረ ጦቢት በእንተ ብሩር ዘአማኅፀነ ኀበ ገባኤል በራጊስ ዘሜዶን፣

በዚያች ቀን የሜዶን አውራጃ በምትሆን በራጊስ ከገባኤል ዘንድ አደራ ያስቀመጠውን የብሩን ነገር ጦቢት አሰበ፤

፪፡ ወሐለየ ወይቤ፣

አሰቦ እንዲህ አለ፤

ናሁ ሰአልኩ ከመ እሙት፣

እነሆ ልሙት ብዬ ለመንሁ፤

ወለምንት ኢይጼውዖ ለወልድየ ጦብያ ከመ እንግሮ ዘእንበለ እሙት፤

ሳልሞት እነግረው ዘንድ ልጄ ጦብያን ለምን አልጠራውም፤

፫፡ ወጸውዖ ወይቤሎ፣

ጠርቶ እንዲህ አለው፤

ወልድየ አመ ሞትኩ ቅበረኒ በሠናይ፣

ልጄ በሞትሁ ጊዜ አክብረህ ቅበረኝ፤

ወዕቀብ እመከ፣

እናትህንም ተንከባከባት፤

ወአክብራ በኵሉ መዋዕለ ሕይወታ።

ባለ በዘመኗ ሁሉ አክብራት፤

ወግበር ላቲ ኵሎ ዘፈቀደት።

የወደደችውን ሁሉ አድርግላት፤

ወኢታኅዝና።

አታሳዝናት፤

፬፤ ተዘከር ወልድየ ከመ ብዙኃ ሕማመ ረከበት ብከ።

ባንተ ምክንያት ብዙ መከራ ተቀብላለችና፤

እንዘ ሀሎከ ውስተ ከርሣ።

በማኅፀኗ ሳለህ፤

ወአመ ሞተት ቅብራ ምስሌየ ውስተ አሐዱ መቃብር።

በሞተችም ጊዜ ከኔ ጋራ ቅበራት፤ አንድም ከኔ ጋራ ደርባት፤

፭፤ ወበኵሉ መዋዕል አ ወልድየ ተዘከሮ ለእግዚአብሔር አምላክነ።

ልጄ ባለ በዘመንህ ሁሉ ፈጣሪ ያችን እግዚአብሔርን አስበው፤

ወኢትፍቅድ አብሶ ወክሂደ ትእዛዙ፤

እሱን መበደል ትእዛዙን ማፍ ረስን አትውደድ፤

ወግበር ጽድቀ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ።

ባለ በዘመንህ ሁሉ በጎ ሥራ ሥራ፤

ወኢትሖር በፍኖተ ዓመፃ፤

በማይገባ ሥራ ጸንተህ አትኑር፤

፮፤ ወእምከመ ገበርከ ለጽድቅ ትሤራህ በኵሉ ፍኖትከ።

በጎ ሥራን ብትሠራት በሥራህ ሁሉ ትከናወናለህ የቀና ይሆናል፤

ወበኵሉ ግብርከ ዘገበርከ።

በምትሠራው ሥራ ሁሉ ሥራህ የቀና ይሆናል፤

ወከማሁ ለኵሎሙ እለ ይገብርዋ ለጽድቅ።

ጽድቅን የሚሠሯት ሰዎች ሁሉ ሥራቸው የቀና ይሆናል፤

፯፤ ወእምንዋይከ ግበር ምጽዋተ።

ከገንዘብህ ሁሉ ምጽዋት ስጥ፤

ወኢትደንግፅ ዓይንከ ሶበ ትገብር ምጽዋተ።

ምፅዋትህን በመፀወትህ ጊዜ አጣለሁ ብለህ አትደንግጥ፤ አንድም ኢትደንፁ ቢል በዓይንህ አትንፈግ።

ወኢትሚጥ ገጸከ እምነ ነዳይ።

ፊትህንም ከድኃ አትመልስ፤

ወእግዚአብሔር ኢይመይጥ ገጾ እምኔከ።

እንዲህ ያደረግህ እንደሆነ እግዚአብሔርም ፊቱን አይመ ልስብህም፤

፰፤ ወአምጣነ ትክል መጠነ ብከ ግበር ምጽዋተ፣

መጠነና አምጣነ አንድ ወገን በገንዘብህ ልክ ስጥ፤ አንድም የተቻለህን ያህል ምጽዋት ስጥ፤

ወእመኒ ውኁድ ኢትደንግፅ ለገቢረ ምጽዋት፣

ጥቂትም ቢሆን ምጽዋት ለመመጽወት አትደንግጥ፤ አንድም ኢትደንፀ ይላል አትንፈግ፤

፱፤ እስመ ሠናየ መዝገበ ትዘግብ ለከ፣

ምጽዋት በጐ ዋጋ ታስጥሃለችና፤

፲፣ እስመ ምጽዋት ታድኅን እሞት በዕለተ ምንዳቤ፣

ምጽዋት በመከራ ቀን ከሞተ ሥጋ ከሞተ ነፍስ ታድናለችና፤

ወኢትወስድ ውስተ ጽልመት፤

ወደመከራ፤ አንድም ወደገሃነም አትወስድም፤

፲፩፣ እስመ ሠናይ ጸጋ ይእቲ ምጽዋት ለእለ ይገብርዋ በቅድመ ልዑል፣

በጌታ ፊት ለሚያደርጓት ሰዎች ምጽዋት በጐ ስጦታ ናትና፤

፲፪፤ ወዑቅ ርእሰከ እ ወልድየ እምኵሉ ዝሙት፣

ልጄ ከዝሙት የተነሣ ለራስህ እወቅ፤

ወቅድም ለከ ነሚአ ብእሲት እምዘርአ አበዊከ፣

አስቀድመህ ካባቶችህ ወገን ሚስት አግባ፣

ወኢታውስብ እምነኪር ለእመ ኢኮነት እምዘመድከ፣

ከዘመዶችህ ወገን ካልሆነች ከባዕድ አታግባ፤

እስመ እምደቂቀ ነቢያት ንሕነ፣

እኛ የደጋጎች ሰዎች ልጆች ነንና፤

ኖኅ ወአብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ እለ እምዓለም አበዊነ፤

እነዚህም ከጥንት ጀምረው የነበሩ አባቶቻችን ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ናቸው፤

ተዘከር ወልድየ ከመ ኵሎሙ ነሥኡ አንስቲየ እምትውልደ አኃዊሆሙ፣

ልጄ ሁሉም ከወንድሞቻቸው ልጆች ሚስት እንዳገቡ አስብ፣

ወተባረኩ ውሉዶሙ ወዘርአሙ ወረስዋ ለምድር፡

ልጆቻቸው የልጅ ልጆቻቸው እንደተባረኩ ይህችንም ዓለም እንደወረሷት አስብ፤

፲፫፤ ወይእዜኒ ወልድየ አፍቅር ቢጸከ፤

አሁንም ልጄ ባልንጀራህን ውደድ፤

ወኢታዕቢ ልበከ እምነ ቢጽከ፣

ከባልጀራህ የተነሣ ልብህን አታ ስታብይ፤

ወእምደቂቀ ሕዝብከ፣

ከወገኖችህ ልጆች፤

ወእምነ አዋልዲሆሙ ንሣእ ለከ ብእሲተ እምኔሆሙ፤

ከሴቶች ልጆቻቸው ወገን ሚስት አግባ፤

እስመ ኀበ ሀለወት ትዕቢት ሀየ ሀሎ ኃሣር፣

ትዕቢት ካለች ዘንድ ተዋርዶ አለና፤

ወብዙኀ ሁከት፣

ብዙ ሁከት አለና፤

ውኀበ ሀለወ ሁከት፣

ሁከትም ካለች ዘንድ፤

ሀየ ሀሎ ተጽናስ ወንዴት፣

ንዴት ችግር አለና፤ አንድም እስመ ኀበ ሀለወ ትዕቢት፣ ትዕቢት ካለ ዘንድ ሁከትም ካለች ዘንድ፤ ሀየ ሀሎ ተጽናስ ወንዴት፣

ችግር ንዴት አለና፣ ራስህን አታስታብይ፤

እስመ እማ ይእቲ፣

የትዕቢት መገኛዋ ይህች ስለሆ ነች፤ አንድም ሁከት ካለች ዘንድ ጽኑእ ንዴት አለና፣ እስመ እማ፣ መገኛዋ ናትና፤

አንድም እስመ እምሰማይ ይላል፤ የፍዳ (የፍርድ) መገኛዋ ከጌታ ዘንድ ነውና፤

፲፬፤ አስቡለከ ሉ ዘተጋነየ ለከ ኢይቢት ኀቤከ፣

የተገዛልህ ሰው ሁሉ ደመወዝ ካንተ ቤት አይደር፤

አላ ሀቦ በጊዜሃ እምዘ ብከ፣

ከዚያው ካለ ገንዘብ በጊዜዋ ጊዜ ስጠው እንጂ፤

ወእምከመ ተቀነይከ ለእግዚአ ብሔር ይፈደፍድ አስብከ፣

ለእግዚአብሔር ብትገዛ ዋጋህ ይበዛልሃል፤

ወዑቅ ርእሰከ፣

ለራስህ እወቅ፤

ወበኵሉ ግብርከ ኩን ጠቢበ ወበኵሉ ግዕዝከ፣

በምትሠራው ሥራህ ሁሉ አዋቂ ብልህ ሁን፤

፲፭፣ ወዘትጸልዕ ለርእስከ ኢትግበር ለመኑሂ፣

ለራስህ የምትጠላውን ለሰው አታድርገው፤

ወይነ ለሰኪር ኢትስተይ፣

ለመስከር ወይን አትጠጣ፤

ወኢትሖር ምስለ ስክርት ውስተ ፍኖትከ፣

በጐዳና ከሰከረች ሴት ጋራ አትሂድ፤ አንድም ምስለ ስክርት ይላል ከሕዝብ ጋራ አትሂድ፤

፲፮፤ ወእምነ እክልከ ሀብ ለርኁብ፤

ከእህልህም ለተራብ ስጥ፤

ወእምነ አልባሲከ ሀብ ለዕሩቅ፤

ከልብስህም ለታረዘ ሰው ስጥ፤

ወእምኵሉ ዘይተርፈከ ግበር ምጽዋተ፤

ከዕለት ምግብ የቀረህን ምጽዋት ስጥ፤

፲፯፤ ወዝሩ እክለከ ላዕለ መቃብረ ጻድቃን፤

እህልህን በከርሠ ርኁባን አኑር፤

ዕደው ጻድቃን የሐልዉ ውስተ ምሳሕከ እንዲል፤ አንድም የነቢያትን መቃብር ሥራ ዋጋ ታገኛለህ፤

ወኢተሀብ ለኃጥአን፤

ለባለጸጎች አትስጥ፤ አንድም በገንዘብህ የኃጥአንን መቃብር አትሥራ፤

፲፰፤ ምክረ ኅሡሥ በኀበ ኵሉ ጠቢባን፤

ካዋቆች ሰዎች ዘንድ ምክርን ሻ፤

ወኢታስትት ምክረ እንተ ትበቍዓከ፤

የምትረባህን፤ የምትጠቅምህን ምክር አትናቅ፤

፲፱፤ ወበኵሉ ጊዜ ባርኮ ለእግዚአብሔር፤

በየጊዜው ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግን፤

ወጸሊ ኀቤሁ ከመ ሥሩሐ ይኩን ፍኖትከ፤

ሥራህ የቀና ይሆን ዘንድ ከሱ ዘንድ ጸልይ፤

ወይሤርሐከ በኵሉ ግብርከ ወበኵሉ ፍናዊከ፤

በምትሠራው ሥራ በሄድህበት ሁሉ ሥራህ ይቀናልሃል፤

እስመ ኵሎሙ አሕዛብ ዘይመክሩ ምክረ ዘኢኮነ እምእግዚአብሔር፤

አሕዛብ የሚመክሩት ምክር ሁሉ ከእግዚአብሔር የተገኘ አይደለምና፤ ካዋቆች ዘንድ ምክርን ሻ፤ አንድም አሕዛብ የሚመክሩት ምክር ከእግዚአብሔር የተገኘ አይደለምና፤ ከንቱ ውእቱ ከንቱ ነው፤ አንድም ከእግዚአብሔር ያልተገኘ ምክርን የሚመክሩ አሕዛብ፤ ከንቱ እሙንቱ፤ ከንቱ ናቸውና ወኀቤሁ ጸሊ ሳለው፤

እንበለ ውእቱ እግዚአብሔር ይሁብ ኵሎ ሠናይቶ፤

በጐውን ሁሉ የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው እንጂ፤

ወለዘፈቀደ ያቴሕቶ በከመ ውእቱ ፈቀደ፤

እሱ እንደወደደ ሊያዋርደው የወደደውን ያዋርዳል፤

ወይእዜኒ ወልድየ ተዘከር ትእዛዝየ፤

ልጄ አሁንም ትእዛዜን አስበው፤

ወኢይደምሰስ እምልብከ፤

ከልቡናህ አይራቅ፤

፳፡ ወይእዜኒ እነግረከ በእንተ መካልየ ብሩር ዐሥርቱ ዘአዕቀብኩ ኀበ ገባኤል ወልደ ግብርያ ዘራጊስ ዘሜዶን፣

አሁንም በራጊስ ዘሜዶን ከግብርያ ልጅ ከገባኤል ዘንድ ያኖርሁትን ያሥሩን መክሊት ነገር እነግርሃለሁ፤

፳፩፡ ወኢትፍራህ ወልድየ በእንተ ንዴትከ፣

ልጄ አጣለሁ ብለህ አትፍራ፤

እስመ ነዳያን ብከ ይነሥኡ በረከተ፣

ነዳያን ካንተ ብዙ በረከትን ይቀበላሉና፤

ለእመ ፈራህኮ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን ከፈራኸው፤

ወኃደገ ኵሎ ኃጢአተከ፣

ኃጢአቱን ከተውህ፤

ወገበርከ ዘያሠምሮ ለእግዚአብሔር በቅድሜሁ፣

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ሥራ በፊቱ ከሠራህ አጣለሁ ብለህ አትፍራ።

## ምዕራፍ ፭

፩፡ ወአውሥአ ጦቢያ ወይቤ፣

ጦቢያ መለሰ፣ እንዲህ አለ፤

እገብር አባ ኵሎ ዘአዘዝከኒ፣

አባቴ ያዘዝከኝን ሁሉ አደርጋለሁ፤

፪፡ ወባሕቱ እፎ እክል ነሢኦቶ ለውእቱ ብሩር ዘኢየአምሮ፣

ነገር ግን አገሩን አላውቅ፣ ሰውን አላውቅ፣ ያንን ብሩን መቀበል እንዴት ይቻለኛል፤

፫፡ ወወሀቦ መጽሐፈ፣

ጦማር ደብዳቤ ጽፎ ሰጠው፤

ወይቤሎ ኅሥሥ ብእሴ ዘየሐውር ምስሌከ፣

አብሮህ የሚሄድ ሰው ፈልግ አለው፤

ወእሁቦ አስቦ እንዘ ሕያው አነ፣

እኔ በሕይወት ሳለሁ ደመወዙን እሰጠዋለሁ፤

ወሑር ንሣእ ዘንተ ብሩረ፣

ሂደህ ብሩን ተቀበል አለው፤

፬፡ ወሖረ ይኅሥሥ ለዘ ብእሴ፣

ሰው ሊፈልግ ሄደ፣

ወረከቦ ለሩፋኤል መልአከ፣

መልአኩ ሩፋኤልን አገኘው፣

ወኢያእመሮ ከመ መልአክ ውእቱ፣

መልአክ እንደሆነ አላወቀውም፤

፭፡ ወይቤሎ ትክልኑ ሐዊረ ምስሌየ ራጊስ ዘሜዶን እመ ተአምር ብሔሮ፣

ሀገሩን ታውቀው እንደሆነ ወደራጊስ ዘሜዶን ከኔ ጋራ አብረህ መሄድ ይቻልሃል አለው፣

፮፤ ወይቤሎ ውእቱ መልአክ አሐውር ምስሌከ፣

መልአኩም ካንተ ጋራ እሄዳለሁ አለው፤

ወፍኖቶሂ አአምር፣

ጐዳናውንም አውቀዋለሁ፤

ውኅበ ገባኤልሂ ነበርኩ፣

ከገባኤልም ዘንድ ነበርሁ አለው፤

፯፤ ወይቤሎ ጦብያ ጽንሐኒ ከመ እንግሮ ለአቡየ ጦቢት፣

ላባቴ ለጦቢት እነግረው ዘንድ ጠብቀኝ አለው፣

፰፤ ወይቤሎ ሑር ኢትጐንዲ፣

ሂድ አትዘግይ አለው፣

ወሖረ ወይቤሎ ለአቡሁ ነዋ ረከብኩ ዘየሐውር ምስሌየ፣

ሂዶ አባቱን ከኔ ጋራ አብሮኝ የሚሄድ ሰው አገኘሁ አለው፤

ወይቤሎ ጸውዖ ኀቤየ ከመ አአምር እምአይ ሕዝብ ውእቱ፣

ከማን ወገን እንደሆነ አውቅ ዘንድ ጠርተህ አምጣው አለው፤

ወእመ ማእምን ለሐዊር ምስሌከ፣

ካንተ ጋራ ለመሄድ የታመነም እንደሆነ አውቅ ዘንድ ጥራው አለው፤

፱፤ ወጸውዖ ወቦአ፤

ጠርቶት ገባ፣

ወተአምኁ በበይናቲሆሙ

እርስ በርሳቸው እንዴት ነህ እንዴት ነህ እየተባባሉ እጅ ተነሳሱ፤

፲፤ ወይቤሎ ጦቢት አንተ እኁየ እምአይ ሕዝብ አንተ፣

አንተ ወንድሜ ከማን ወገን ነህ አለው፤

ወእምአይ ብሔር አንተ፤

አንተስ ከማን ሀገር ነህ አለው፤

፲፩፤ ወይቤሎ መልአክ ሕዝበየኑ ወብሔርየኑ ተኃሥሥ፣

ሀገሬን ወገኔን ትፈልጋለህን፤

አው አስቦ ዘየሐውር ምስለ ወልድከ፣

ወይስ ከልጅህ ጋራ የሚሄድ ሰው ደመወዙን ነው ማለት ከዋዩ እንጂ ከወገኔ ምን አለህ፣

ወይቤሎ ጦቢት እፈቅድ አንተ እኁየ አእምር ዘመደከ ወስመከ፣

ጦቢትም አንተ ወንድሜ ዘመድህን ስምህን አውቅ ዘንድ እወዳለሁ አለው፤

፲፪፤ ወይቤሎ አንሰ አዛርያ ዘመደ አናንያ ዓቢይ እኁከ፣

እኔስ የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ዘመድ አዛርያ እባላለሁ አለው፤

፲፫፤ ወይቤሎ ዳኅንኑ አንተ እኁየ፣

አንተ ወንድሜ ደህና ነህ አለው፤

ወኢትኒሰኒ እስመ ኃሠሥኩ አእምር ሕዝበከ ወብሔረከ፣
ሀገርህን፣ ወገንህን አውቅ ዘንድ መርምሬሃለሁና በዚህ አትን ቀፈኝ።
ወአማን ባሕቱ እምሠናይ ዘመድ አንተ ወቡሩክ፣
ነገር ግን አንተስ በጐ ሰው ከከበረ ወገን ነህ አለው።
ወአእምሮ አነ ለአዛርያ ደቂቀ ሴምዩ ዓቢይ፣
ደግ የሚሆን የሴምዩን ልጅ አዛርያን አውቀዋለሁ።
ወሖርነ ምስሌሆሙ ኅቡረ ኢየሩሳሌም ከመ ንስግድ፣
እንሰግድ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ከነሱ ጋራ ባንድ ሄደን ነበር።
ወወሰድነ በኵረነ ወአሥራተ እክልነ፣
አሥራቱን በኵራቱን እንወስድ ነበረ።
ወኢአበስነ አበሳ አበዊነ፣
አባቶቻችን የሠሩትን አልሠ ራንም፣
ወአንተሰ እምነ ዓቢይ ሥርው አንተ እኁየ፣
አንተ ወንድሜ አንተስ ከደግ ሰው ወገን ነህ።
፲፩፤ ወባሕቱ ንግረኒ ምንተ ነሀብ አስበከ፣
ነገር ግን ዋጋህን ምን እንሰጥህ ዘንድ ንገረኝ።

ድርከሙኑ ለለዕለትከ፣
ዕለት ዕለት አንዳንድ ድሪም እንስጥህን።
ወሲሳይከ ምስለ ወልድየ፣
ምግብህስ ከልጄ ጋራ ነው፣
፲፪፤ ወእዌስከ አስበከ በዲበ አስብከ ለእመ ዳኅነ አቶክሙ፣
በደኅና ከተመለሳችሁ ቢያንስ ህም ደመወዝህን እጨምር ልሃለሁ።
፲፫፤ ወአኅለቁ ከመዝ፣
እንዲህ አድርገው ነገር አቆሙ፣
ወይቤሎ ጦቢት ለጦብያ ወልዱ ተደለው ከመ ትሖር፣
ጦቢት ልጁ ጦብያን ትሄድ ዘንድ ተዘጋጅ አለው።
ወተሠርሑ፣
ጎዳናችሁን አቅኑ።
ወአስተዳለወ ወልዱ ስንቆሙ ለፍኖት፣
ለጐዳና የሚሆን ስንቃቸውን ልጁ አዘጋጀ።
ወይቤሎ አቡሁ ሑር ምስለ ዝንቱ ብእሲ፣
አባቱ ከዚህ ሰው ጋር ሂድ አለው።
ወእግዚአብሔር ዘይነብር ውስተ ሰማይ ይሠርሕ ፍኖተክሙ።
በሰማይ የሚኖር እግዚአብ ሔር ጐዳናችሁን ያቅናላችሁ።

ወመልአኩ ይሑር ምስሌክሙ፤

መልአኩ ከእናንተ ጋራ አብሮ ችሁ ይሂድ፤ መንፈስ ቅዱስ ያናግረዋል፤

ወወጽኡ ክልኤሆሙ ወሖሩ፣

ሁለቱ ወጥተው ሄዱ፤

ወተለዎሙ ከልበ ወልዶሙ፣

የልጃቸው ውሻ ተከተላቸው፤

፲፯፣ ወበከየት ሐና እሙ፣

እናቱ ሐና አለቀሰች፤

ወትቤሎ ለጦቢት ለምንት ፈነውከ ለወልድየ፣

ጦቢትን ልጄን ለምን ሰደድከው አለችው፤

አኮኑ ውእቱ በትርነ እንተ ውስተ እዴነ ዘይወጽእ ቅድሜነ፣

በፊት በፊታችን የሚሄድ የእጃችን በትር አይደለምን፤

፲፰፣ ብሩር ለይጥፋዕ፣

ብር ያመጣ ዘንድ ሄዷል ቢላት እሷም ብሩስ እልም ድርግም ይበል አለችው፤ አንድም እንዲ ላት አውቃ ብሩስ እልም ድርግም ይበል አለችው፤

፲፱፣ ወቢዛሁ ለወልድየ ይኩን ዘወሀበነ እግዚአብሔር ዘቦቱ ነሐዩ፣

ተድላ ደስታ የምናደርግበት እግዚአብሔር የሰጠን የልጄ ለውጥ ይሁነው፤

፳፣ ወይቤላ ኢትትኀለፊ እኅትየ፣

ጦቢትም እኅቴ እልፍ እልፍ ብለሽ አትናገሪ አላት፤ አንድም ኢትትለኃፊ እኅትየ፣ እኅቴ አትዘኚ አላት፤ ወአልቦሙ ትኅላፈ ነገር እንዲል፣

ዳኅነ የአቱ፣

ልጅሽ ደኅና ይመለሳል፤

ወትሬእዪዮ በአዕይንትኪ፣

በዓይንሽ ታይዋለሽ፤

፳፩፣ እስመ መልአከ እግዚአብሔር የሐውር ቅድሜሁ፣

መልአከ እግዚአብሔር በፊት በፊቱ ይሄዳልና፤

ወይሜርሖ ፍኖቶ፣

ጉዳናውንም ያቀናለታልና፤

ወየአቱ ዳኅነ፣

በደኅና ይመለሳል፤

ወኃደገት ብካየ ሐና፣

ሐና ልቅሷዋን ተወች::

## ምዕራፍ ፮

፩፤ ወእንዘ የሐውሩ ፍኖቶሙ በጽሑ በጣኔስ ውስተ ተከዚ ምሴተ፣

ጉዳናቸውን ሲሄዱ በመሸ ጊዜ ከፈሳሽ ውሀ ተከዚ ደረሱ፤

ወቤቱ በህየ፣

በዚያ አደሩ፤

፪፡ ወወረደ ውእቱ ወልድ ይትሐፀብ፣

ይታጠብ ዘንድ ጦቢያ ወደወንዝ ወረደ።

ወሠረረ ዓሣ ዐቢይ እምውስተ ተከዚ፣

ከዚያ ከፈሳሽ ውሀ ዓሣው ወደሱ እየተወረወረ መጣ።

ወፈቀደ የሐጦ ለውእቱ ወልድ፣

ጦቢያን ሊውጠው ወደደ፣ ለሱ ስለመሰለው ነው።

፫፡ ወይቤሎ መልአክ አኀዝ ለውእቱ ዓሣ፣

መልአኩም ይህን ዓሣ ያዘው አለው።

ወአኀዞ ለዓሣ ውእቱ ወልድ፣

ጦቢያ ዓሣውን ያዘው።

ወአውጽአ ውስተ ምድር፡

ወደየብስ አወጣው።

፬፡ ወይቤሎ ዝኩ መልአክ ምትሮ ለውቱ ዓሣ፣

መልአኩም ይህን ዓሣ እረደው አወራርደው አለው።

ወንሣእ ልቦ ወከብዶ ወሐሞቶ፣

ልቡን ጉበቱን ሐሞቱን ያዝ።

ወአጽንዕ ዓቂቦቶ፣

አጽንተህ ጠብቀው።

፭፡ ወገብረ ውእቱ ወልድ በከመ አዘዞ መልአክ፣

ጦብያም መልአኩ እንዳዘዘው አደረገ።

ወዓሣሁሰ ጠበሱ ወበልዑ፣

ዓሣውን ጠብሰው በሉ።

ወጌሡ ክልኤሆሙ፣

ሁለቱም ገስግሠው ሄዱ።

ወበጽሑ በጣኔስ፣

ጣኔስ ደረሱ የተላለፈ ነው። ጠበሱ ወበልዑ፣ ወጌሡ ሲል ነው።

፮፡ ወይቤሎ ዝኩ ወልድ ለመልአክ፣

ጦብያ መልአኩን እንዲህ አለው።

አንተ እኁየ አዛርያ ምንት ውእቱ ከብዱ ወልቡ ወሐሞቱ ለዝንቱ ዓሣ፣

አንተ ወንድሜ አዛርያ የዚህ አሣ ጉበቱ ልቡ ሐሞቱ ምን ይሆናል አለው።

፯፡ ወይቤሎ ልቡ ወከብዱ ለእመቦ ዘየሐምሞ ጋኔን እኩይ፣

ክፉ ጋኔን የሚጥለው ሰው ቢኖር።

ዘንተ ያጠይሱ ቅድሜሁ ለውእቱ ብእሲ፣

ለዚያ ለታመመው ሰው በፊቱ ያጤሱለት እንደሆነ፣

ወእመኒ ብእሲት፣

ሴትም ብትሆን በፊቷ ያጤሱ ላት እንደሆነ፤

ወኢየሐምም እንከ፤

ከዚያ ወዲያ አይታመምም፤

፰፤ ወሐሞቶስ ይኩሕልዎ ለብእሲ ዘቦቱ ጢስ ውስተ አዕይንቲሁ፣

ሐሞቱን ግን ባይኑ ብግር ብልዝ ያለበትን የኳሉት እንደሆነ፤

ወየሐዩ፣

ይድናል፤

፱፤ ወሶበ ቀርቡ ኀበ ራጊስ፣

ወደራጊስ በቀረቡ ጊዜ፤

ወይቤሎ ውእቱ መልአክ አንተ እኁየ ዮምኬ ኀበ ራጉኤል ነኀድር፣

መልአኩም አንተ ወንድሜ ዛሬ ከራጉኤል ዘንድ እናድራለን አለው፤

፲፤ ወአዝማዲከ ውእቱ፣

እሱም ዘመድህ ነው፤

ወቦ አሐቲ ወለት ወስማ ሣራ፤

ስሟ ሣራ የምትባል አንዲት ልጅ አለችው፤

ወእትናገርኑ በእንቲአሃ የሀቡከ ትኩንከ ብእሲተ፣

ሚስት ልትሆንህ ይሰጡህ ዘንድ ስለርሷ ልንገርልህን፤

፲፩፤ እስመ ለከ ይበጽሐከ ርስታ፣

ላንተ ትገባሃለችና፤

ወአንተ ሀሎከ እምነ አዝማዲሃ፣

ከዘመዶቿ ወገን አንተ አለህና፤

ወወለትኒ ሠናይት ወጠባብ፣

ልጅቱም መልከ መልካም አዋቂ ልባም ናት፤ ይኸውም ልማድ ነው፤ ላማጭ እንዲህ ብሎ መናገር፤

፲፪፤ ወይእዜኒ ስምዓኒ፣

አሁንም ስማኝ፤

ወእትናገር ለአቡሃ፣

ላባቷ ልንገረው

ወሶበ ገባዕነ እምነ ራጊስ ንገብር በዓለ፤

ከራጊስ በተመለስን ጊዜ ሠርግ እናደርጋለን፤

እስመ ኢይገብር የሀባ ራጉኤል ለካልዕ ሰብእ

ራጉኤል ለሌላ ሰው ይሰጣት ዘንድ አይወድምና፤

በእንተ ሕገ ሙሴ፣

የሙሴን ሥርዓት ስለ መፈጸም፤

ወእምአብደረ ትሙት፤

ሌላ ከሚያገባት ብትሞት ይወ ዳልና፤

እስመ ርስታ ለከ ይበጽሐከ እምኵሉ ሰብእ፣

ከሰው ሁሉ ላንተ ትገባሃለችና፤

፲፫፤ ወይቤሎ ዝኩ ወልድ ለውእቱ መልአክ፣

ጦቢያ መልአኩን እንዲህ አለው፤

አንተ እኁየ አዛርያ ሰማዕኩ አነ ከመ አስተዋስብዋ ለይእቲ ወለት ለሰብእ ዕደው፣

አንተ ወንድሜ አዛርያ ይህችን ልጅ ለሰባት ወንዶች እንዳጋቧት ሰምቻለሁ፤

ወኩሎሙ ሞቱ አመ ኩብካብ፣

ሁሉም በሠርግ ቀን ሞቱ፤

፲፬፤ ወይእዜኒ ባሕቲትየ አነ ለአቡየ፤

አሁንም ላባቴ እኔ ብቻ ነኝ፤

እፈርህ ሶበ ቦእኩ ኢይሙት፣

እንዳልሞት ብዬ እፈራለሁ፤

ወኢይወርድ ሕይወቶሙ ለአቡየ ወእምየ በሃዕር፣

የእናት ያባቴ አኗኗር በኔ ምክንያት ወደመቃብር እንዳላወርዳቸው ብዬ እፈራለሁ፤

ወአልቦሙ ካልዕ ወልድ ዘይቀብሮሙ፣

የሚቀብራቸው ሌላ ልጅ የላቸውም፤

፲፭፤ ወይቤሎ ውእቱ መልአክ ኢትዜክርኑ ቃለ ዘአዘዘከ አቡከ፣

መልአኩ አባትህ ያዘዘህን ቃል አታስብም አለው፤

ከመ ትንሣእ ለከ ብእሲተ እምአዝማዲከ፣

ከዘመዶችህ ወገን ሚስት ታገባ ዘንድ፤

ወይእዜኒ ስምዐኒ አንተ እኁየ፣

አሁንም አንተ ወንድሜ ስማኝ፤

ወበእንተ ጋኔንሰ ኢየኀዝንከ፣

ስለጋኔኑ ግን አያሳዝንህ፤

እስመ በዝንቱ ሌሊት ትትወሀብ ለከ ብእሲት እምአዝማዲከ፣

በዚች ሌሊት ከዘመዶችህ ወገን የምትሆን ሚስት ሁና ትሰጥሃለች፤

፲፮፤ ወሶበ ቦእከ ውስተ ጽርሕክ ንሣእ ለከ ሕራረ ዕጣን፣

ወደቤትህ በገባህ ጊዜ ሕራሪ ዕጣን አምጣ፤

ወደይ እምነ ከብዱ ወልቡ ለዝኩ ዓሣ፣

ከዓሣው ከጉበቱ፣ ከልቡ ጨምረህ፤

ወአጢስ ቦቱ፣

አጢስበት፣

፲፯፤ ወሶበ ጼነዎ ለውእቱ ጋኔን ይጐይይ፣

ለዚያ ለጋኔኑ በሸተተው ጊዜ ይሸሻል፤ አንድም ወሶበ ጼነወ ውእቱ ጋኔን ይጐይይ በሸተተው ጊዜ ይህ ጋኔኑ ይሸሻል፤ አንድም ወሶበ ጼነዎ ውእቱ፣ ይህ በሸተተው ጊዜ ጋኔን ጕየ ሸሸ፤

ወኢይገብእ ለዓለም፣

ለዘለዓለሙ አይመለስም፤

ወሶበ ቦእከ ኀቤሃ ጽርሑ ክልኤክሙ ኀበ እግዚአብሔር መሐሪ፣

እርሷ ወደ አለችበት በገባህ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሁለታ ችሁም ለምኑ፤

ወያድኅነክሙ፣ ወይምሕረክሙ፣

ያድናችኋል ይቅር ይላችኋል፤

ወኢትፍርሁ እንከ፣

እንግዲህ ወዲህ ግን አትፍሩ፤

እስመ ኪያክሙ አስተዳለወ እምነ ዓለም፣

ከሰው ሁሉ እናንተን ባልና ሚስት ለመሆን አዘጋጅቷልና፤

ወአንተ ታድኅና፣

አንተ ታድናታለህ፤

ወተሐውር ምስሌከ፣

ካንተ ጋራ ትሄዳለች፤

ወእብለከ ከመ ትረክብ ውሉደ እምኔሃ፤

ከሷ ልጅ እንድትወልድ እነግር ሃለሁ፤

ወሰሚዖ ጦብያ አንከረ፣

ጦብያ ይህን ሰምቶ አደነቀ፤

ወተለዋ ነፍሱ ኀቤሃ ጥቀ፣

ኪያሃ ሲል ነው፤ ልቡናው እሷን ተከተለ፤

ወበጽሑ ውስተ በጣኔስ፣

በጣኔስ ደረሱ።

# ምዕራፍ ፯

## ጉባዔ

፩፤ ወቦኡ ቤተ ራጉኤል፣

ከራጉኤል ቤት ገቡ፤

ወተቀበለቶሙ ሣራ፣

ሣራ ተቀበለቻቸው፤

ወአስተፍሥሐቶሙ፣

ደኅና ናችሁ ብላ ደስ አሰኘቻ ቸው፤

ወከማሁ እሙንቱኒ ላቲ፣

እነዚያም ደኅና ነሽ አሏት፤

ወአብአቶሙ ቤተ፣

ወደቤት አገባቻቸው፤

፪፤ ወይቤላ ራጉኤል ለብእሲቱ እድና፣

ራጉኤልም ሚስቱን እድናን እንዲህ አላት፤

ዕፁብ ዝንቱ ወልድ፣

ይህ ልጅ ድንቅ ነው አላት፤

ይመስሎ ለጦቢት ዘእምአዝማድየ፤

ከዘመዶቼ ወገን የሚሆን ጦቢትን ይመስለዋል፣

፫፤ ወይቤሎሙ ራጉኤል እምአይቴ አንትሙ አኃውየ፣

እናንተ ወንድሞቼ ከወዴት ናችሁ አላቸው፤

ወይቤልዎ እምደቂቀ ንፍታሌም እለ ተጼወዉ ነነዌ፣

ተማርከው ወደ ነነዌ ከሄዱት ከንፍታሌም ልጆች ወገን ነን አሉት፣

፬፤ ወይቤሎሙ ራጉኤል ተአምርዎኑ ለጦቢት እኁየ፣

ራጉኤልም ወንድሜ ጦቢትን ታውቁታላችሁን አላቸው፤

፭፤ ወይቤልዎ እወ ነአምሮ፣

አዎን እናውቀዋለን አሉት፤

ሕያውኑ ወዳኅንኑ፣

ከጉልበት ነውን ደኅና ነውን አላቸው፤ አዎን ደኅና ነው ገና ከጉልበት ነው አሉት፤

ወይቤሎ ጦቢያ አቡየ ውእቱ፣

ጦቢያ አባቴ ነው አለው፤

፮፤ ወሠረረ ራጉኤል ወሰዓሞ ወበከየ፣

ራጉኤልም ተነሥቶ ሳመው አለቀሰ፣

፯፤ ወባረኮ፣

መረቀው፤

ወይቤሎ ወልደ ብእሲ ብሩክ አንተ፣

አንተስ የደግ ሰው ልጅ ነህ አለው፤

ወነገሮ ከመ ጠፍአ አዕይንቲሁ ለጦቢት፣

የጦቢት ዓይኑ እንደጠፋ ነገረው፤

ወሰበ ሰምዐ ከመ ተኃጕለ አዕይንቲሁ ራጉኤል ተከዘ ወበከየ፤

ራጉኤልም የጦቢት ዓይኑ እንደጠፋ በሰማ ጊዜ አዘነ፣ አለቀሰ፣

፰፤ ወከማሁ እድናሂ ብእሲቱ፣

እድናም አዘነች፣ አለቀሰች፤

ወሣራሂ ወለቱ፣

ልጁ ሣራም አለቀሰች፤

ወተቀበልዎሙ በትፍሥሕት፣

በተድላ በደስታ ተቀበሏቸው፤

ወጠብሑ አባግዐ፣

በጉን አረዱ፤

ወአቅረቡ ሎሙ፣

አቀረቡላቸው፣

ወመስየ በሕቁ፣

ፈጽሞ መሸ፤

ወይቤሎ ጦቢያ ለአዛርያ አንተ እኁየ አዛርያ ተናገር በእንተ ዘትቤለኒ በፍኖት፣

ጦቢያ አዛርያን እንዲህ አለው፤ አንተ ወንድሜ በጐዳና የነገርኸኝን ነገር ንገረው፣

ወይሕልቅ ነገሩ፣

ይህ ነገሩ ይለቅ፤

፱፤ ወዘንተ ሰሚዖ ራጉኤል እንዘ ይትናገሮ ጦቢያ ለመልአኩ፣

ጦቢያ መልአኩን ሲናገረው ራጉኤል ሰምቶ፤

ወይቤሎ ለጦብያ ብላዕ ወስተይ ምዕረ ወተፈሣሕ፤

ራጉኤል ጦብያን ብላ ጠጣ ደስ ይበልህ አለው።

፯፣ እስመ ለከ ይእቲ ወለትየ፤

ይህች ልጄ ላንተ ትገባለችና።

ወአንተ ትነሥእ፤

አንተ ትወስዳታለህ።

ወአነ እነግር ጽድቃ ለዛቲ ወለትየ።

የዚች የልጄን እውነተኛ ነገሯን እነግራችኋለሁ፤

አስተዋሰብክዋ ማንኛ፤ አንድም እውነተኛ ነገሯን እነግራችኋለሁ ብሎ።

፲፩፣ ለዛቲ ወለትየ አስተዋሰብክዋ ለሰብአቱ ዕደው።

ይህችን ልጄን ለሰባት ወንዶች አጋባኋት።

ወእምከመ በኡ ኀቤሃ ይመውቱ በሌሊት፤

ከእሷ ዘንድ ከደረሱ በኋላ ሌሊት ይሞታሉ፤

ወባሕቱ ብላዕ ወተፈሣሕ ምዕረ፤

ነገር ግን አንድ ጊዜ በልተህ ደስ ይበልህ።

ወይቤ ጦብያ ኢይጥዕም ወኢምንተኒ እስከ ታሐልቁ ወታቀውሙ ሊተ ነገርየ፤

ጦብያ እንዲህ አለ፤ ለነገሬ ውል እስክታቆሙልኝ ድረስ ምንም ምን አልቀምስም አለ፤

፲፪፣ ወይቤሎ ራጉኤል ንሣእ እምይእዜሰ ዘበሕጉ፤

ራጉኤልም ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ሥርዓቱ ውሰዳት አለው።

፲፫፣ እስመ እኁሃ አንተ፤

አንተ ወንድሟ ነህና።

ወይእቲኒ ብእሲትከ፤

እሷም እንትህ ናትና ውሰድ፤

ወእግዚአብሔር መሐሪ ይሠርሕክሙ በእንተ ዘትሜኒ፤

መሐሪ የሚሆን እግዚአብሔር ወደበጐው ነገር ያቅናላችሁ፤

፲፬፣ ወጸውዓ ለሣራ ወለቱ፤

ልጁን ሣራን ጠራት።

፲፭፣ ወአኃዛ እዴሃ ወመጠዋ ለጦብያ ትኩኖ ብእሲተ፤

ሚስት ትሆነው ዘንድ እጇዋን ይዞ ለጦቢያ ሰጠው።

ወይቤሎ ናሁ ንሣእ በሕገ ሙሴ፤

በሙሴ ሥርዓት እነሆ ውስድ አለው።

ወአዕትዋ ኀበ አቡከ፤

ከአባትህ ዘንድ አግባት።

ወባረከሙ፤

መረቃቸው።

፲፮፣ ወጸውዓ ለእድና ብእሲቱ፤

ሚስቱን እድናን ጠርቶ።

ወነሥአ መጽሐፈ ውትመ፤

ዕኩል ከብቴን ሰጥቻለሁ ብሎ አተመ።

ወአኃዙ ይብልዑ፤

ይበሉ ጀመረ፣

ወጸውዓ ለእድና ወይቤላ፣

እድናን ጠርቶ እንዲህ አላት፤

አንቲ እኅትየ አስተዳልዊ ካልዓ ጽርሐ ወአብኢያ፣

አንቺ እኅቴ ሜገላውን አዘጋጅተሽ አግቢያት፤

፲፪፤ ወገብረታ በከመ ይቤላ፣

እንዳላት አደረገች፤

ወአብአታ ህየ፣

ከሜገሏዋ አገባቻት፣

ወበከየት፣

አለቀሰች ፤

ወአውከፈት አንብዓ ወለታ፤

ልጇ እንባዋን ወደ እግዚአ ብሔር አቀረበች፤ አንድም ወአውከፈት አንብዓ ወለታ ይላል፣ የልጇን እንባ ሚሰሰች፤ ጠረገች፤

፲፫፤ ወትቤላ ተአመኒ ወለትየ ከመ እግዚአ ሰማይ ወምድር ይሁበኪ ትፍሥሕተ ወኃሤተ ህየንተ ኃዘንኪ፣

ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ጌታ ስለኃዘንሽ ፋንታ ተድላውን ደስታውን እንዲሰጥሽ ልጄ እመኚ አለቻት።

# ምዕራፍ ፲፩

፩፤ ወሶበ አሕለቁ ተደሮ አብእዎ ኀቤሃ ለጦቢያ፣

በልተው ከጨረሱ በኋላ ጦቢያን እሷ ካለችበት አገቡት፤

፪፤ ወሶበ ቦአ ተዘከረ ቃሎ፣

ከእዚያ በገባ ጊዜ ሩፋኤል የነገረውን ነገር አሰበ፤

ወነሥአ ሕራረ ዕጣን ወወደየ እምነ ልቡ ወከብዱ ለዝኩ ዓሣ፣

ሕራረ (የደቀቀ) ዕጣኑን ከአሣው ከጉበቱ ጨምሮ፤

ወአጤሰ፣

አጤሰው፤

፫፤ ወሶበ ጼነዎ ጼናሁ ለዝኩ ጋኔን፣

መዓዛው ለዚያ ለጋኔኑ በሸተተው ጊዜ ሸሸ፤ አንድም ወሶበ ጼነዎ ጕየ ዝኩ ጋኔን፤ አንድም ወሶበ ጼነወ ዝኩ፣ ይህ መዓዛው በሸተተው ጊዜ ጋኔን ጐየ በል፤

እስከ ላዕላይ ደወለ ግብጽ፣

እስከ ላዕላይ ግብጽ ድረስ ሸሸ፤

ወዓሠሮ ዝኩ መልአክ ለውእቱ ጋኔን፣

መልአኩ ይህንን ጋኔን አሥሮ ከመሬት ቀበረው፤

፬፤ ወሶበ ተዓደዉ ክልኤሆሙ፣

ሁለቱ በተቀዳደሙ ጊዜ አንድም፤ ወሶበ ተአፅው ክልዔሆሙ ውስተ ቤት፤

ሁለቱም ከቤት በገቡ ጊዜ፤

ተንሥአ ጦቢያ እምነ ዓራቱ፣

ጦቢያ ካልጋው ተነሣ፤

ወይቤላ ተንሥኢ እኅትየ ንጸሊ ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይሣሃለነ፣

እኅቴ ተነሺ ይቅር ይለን ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንለምን አላት፤

፭፤ ወአኃዘ ጦቢያ እንዘ ይብል ቡሩክ አንተ እግዚአ አምላክ አበዊነ፣

ያባቶቻችን ፈጣሪ አቤቱ ክቡር ምስጉን ነህ እያለ ያመሰግን ጀመረ፤

ወይትባረክ ስምከ ቅዱስ፣

ጽኑ ክቡር የሚሆን ስምህ ይክበር ይመስገን፤

ወይሴባሕ ለዓለመ ዓለም፣

ለዘለዓለም ይክበር ይመስገን፤

ይባርኩከ ሰማያት፣

ሰማያት ሁሉ ያመስግኑሃል፤

ወኵሉ ዘፈጠርከ፣

የፈጠርሃቸው ሁሉ ያመሰግ ኑሃል፤

አንተ ገበርኮ ለአዳም፤

አዳምን የፈጠርኸው አንተ ነህ፤

፮፤ ወወሀብኮ ሔዋንሃ ትኩኖ ብእሲተ፣

ሚስት ትሆነው ዘንድ ሔዋንን ሰጠኸው፤ አንድም ከመ ትርድአ ትረዳው ዘንድ፣

ወከመ ታዕርፎ፣

ታሳርፈው ዘንድ፤

ወእምኔሆሙ ተወልደ ዘርአ ዕጓለ እመሕያው፣

ከነሱ ሰው ሁሉ ተወለደ፤

አንተ ትቤ ኢኮነ ሠናየ የሃሉ ብእሲ ባሕቲቱ፣

አዳም ብቻውን ይኖር ዘንድ አገባብ አይደለም አልህ፣

አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘትረድኦ፤

የምትረዳው ሔዋንን እንፍጠ ርለት እንጂ አልህ፤ በአዳም ባሕርይ አለችና ዘይረድኦ አለ፤ አንድም እሱ የእፍአውን እሷ የውስጡን ትረዳዋለችና፣

፯፤ ወይእዜኒ እግዚኦ እንበይነ ዝሙት ዘእነሥኣ ለዛቲ ብእሲት እኅትየ፣

አቤቱ ይህችን እኅቴን የምወስ ዳት ስለ ዝሙት አይደለም፣

አላ በጽድቅ፤

ይቅርታህን ስደድልኝ እንጂ፤ አንድም ስለ ዝሙት የምወስ ዳት አይደለምና፣

ፈኑ ሣህለከ ላዕሌየ ወላዕሌሃ፣

ለኔም ለሷም ይቅርታን ላክልን ስደድልን፤

ከመ ንትፈሣሕ፣

ደስ ይለን ዘንድ፤ አንድም ንትራሳሰ እንረጃጅ ዘንድ፣ አንድም ንትራዳእ እንረዳዳ ዘንድ፣

፰፤ ወትቤ ምስሌሁ አሜን፣
ከሱ ጋራ አሜን አለች፤
፱፤ ወቤቱ ክልኤሆሙ ኀቡረ በይእቲ ሌሊት፣
በዚያች ሌሊት ሁለቱም ባንድ አደሩ፤
ወእምዝ ተንሥአ ራጉኤል፣
ከዚህ በኋላ ራጉኤል ተነሣ፤
ወሖረ ወከረየ መቃብረ፣
ሂዶ መቃብር ቆፈረ፤
፲፤ እንዘ ይብል የኒ ይመውት ውእቱኒ፣
ይኸም ወይ ይሞት ይሆናል ብሎ፤
፲፩፤ ወገብአ ራጉኤል ቤቶ ወይቤላ ለአድና ብእሲቱ፣
ራጉኤል ወደቤቱ ተመልሶ እድና ሚስቱን እንዲህ አላት፤
፲፪፤ ፈንዊ አሐተ ወለተ ትርአዮ እመሕየው ውእቱ፣
ደኅና እንደሆነ ታየው ዘንድ አንድ ልጅ ስደጂ አላት፤
ወእመ አኮ ንቅብሮ እንዘ አልቦ ዘየአምሮ መኑሂ፣
ሙቶም እንደሆነ ማንም ማን የሚያውቀው ሳይኖር እንቀብ ረው ዘንድ፤
፲፫፤ ወሖረት ይእቲ ወለት ወአርኃወት ኆተ፣
ያች ልጅ ሄዳ ደጁን ከፈተች፤
ወረከበቶሙ ይስክቡ ክልኤሆሙ፣
ሁለቱም ሲጨዋወቱ አገኘቻ ቸው፤
፲፬፤ ወገብአት ወአይድዐቶሙ ከመ ሕያዋን እሙንቱ፣
ተመልሳ ደኅና እንደሆኑ ነገረ ቻቸው፤
፲፭፤ ወባረኮ ራጉኤል ለእግዚአ ብሔር፣
ራጉኤል እግዚአብሔርን አመሰ ገነው፤
ወይቤ ቡሩክ አንተ እግዚኦ በኵሉ በረከት ንጽሕት ወቅድስት፣
ክብርት ንጽሕት በምትሆን ምስጋና አቤቱ አንተ ክቡር ምስጉን ነህ፤
ወይባርኩከ ቅዱሳኒከ በኵሉ ግብርከ፣
በሠራኸው ሥራ ሁሉ ሊቃነ መላእክት ያመሰግኑሃል፤
ወኵሎሙ መላእክቲከ፣
ሠራዊተ መላእክት ያመሰግ ኑሃል፤
ወኅሩያኒከ ይባርኩከ በኵሉ ዓለም፣
የመረጥሃቸው ጻድቃን በዓለሙ ሁሉ ያመሰግኑሃል፣
፲፮፤ ቡሩክ አንተ እግዚኦ እስመ አስተፍሣሕከኒ፣
ደስ አሰኘተኸኛልና አቤቱ አንተ ክቡር ምስጉን ነህ፤

ወበከመ ኢተኃዘብኩ ኮነኒ፣

ያላሰብሁት ተደርጐልኛልና፣ አንድም ያሰብሁት አልተደረ ገብኝምና፤

አላ በከመ ብዙኀ ምሕረትከ ገበርከ ላዕሌየ፣

እንደቸርነትህ ብዛት ይቅር ታህን ለኔ አደረግህልኝ እንጂ፤

፲፯፡ ቡሩክ አንተ እግዚኦ እስመ ተሣሀልኮሙ ለክልኤቱ ባሕታ ውያን፣

ጦቢትንና ሣራን ይቅር ብለሃቸ ዋልና አንተ አቤቱ ክቡር ምስጉን ነህ፤

ወገበርከ ሎሙ እግዚኦ ሠናይተከ፣

አቤቱ ቸርነትህን አድርገህ ላቸዋልና፤

ከመ ይፈጽሙ ሕይወቶሙ በዳኅና ወበፍሥሓ በምሕረትከ፣

በቸርነትህ በተፈጥሮ የተሰጣ ቸውን ዘመን በደኅና በደስታ ይፈጽሙ ዘንድ፤

፲፰፡ ወእምዝ አዘዞሙ ለአግብርቲሁ ይድፍኑ ገቢተ መቃብረ፣

ከዚህ በኋላ ያን መቃብሩን ይደፍኑ ዘንድ ባሮቹን አዘዛ ቸው፤

፲፱፡ ወገብረ ሎሙ በዓለ ዐሡረ ወረቡዐ መዋዕለ፣

ዐሥራ አራት ቀን በዓል አደረገ ላቸው፤

፳፡ ወእምዝ አምሐሎ ራጉኤል ለጦቢያ ከመ ኢይፃእ ወኢይሑር እስከ ይትፌጸም መዋዕል ዐሡር ወረቡዕ ዘመርዓ፣

ከዚህ በኋላ ሠርግ የሚደረ ግባቸው ዐሥራ አራት ቀን እስኪፈጸም ድረስ ራጉኤል ጦብያን ከዚያ ወጥቶ ወደሌላ እንዳይሄድ አማለው፤

፳፩፡ ወእምድኅረ ዝንቱ ይሑር ወይንሣዕ መንፈቀ ንዋዩ፣

ከዚህ በኋላ የገንዘቡን እኩሌታ ይዞ ይሄድ ዘንድ፤

ወይሑር በዳኅን ኀበ አቡሁ፣

በደኅና ካባቱ ይሄድ ዘንድ፤

ወዘተርፈሰ እምድኅረ ሞቱ ውእቱ ወብእሲቱ ይንሥኡ፤

የተረፈውን ገንዘብ ግን እሱ ሚስቱ ከሞቱ በኋላ ይወስዱ ዘንድ፤ አንድም ከሞቱ በኋላ እሱ ሚስቱ ይወስዱ ዘንድ።

## ምዕራፍ ፱

፩፡ ወጸውዖ ጦቢያ ለሩፋኤል ወይቤሎ አንተ እኁየ አዛርያ ንሣእ ምስሌከ ፬ተ ደቂቀ ወአግማለ፣

ጦቢያ ሩፋኤልን ጠርቶ እንዲህ አለው፤ አንተ ወንድሜ አዛርያ ሁለት ብላቴኖችንና ግመሎችን ይዘህ፤

፪፡ ወሑር ራጊስ ዘሜዶን ኀበ ገባኤል፤

ከገባኤል ዘንድ የሜዶን አውራጃ ወደምትሆን ወደራጊስ ሂድ፤

ወንሣእ አሥርተ መክሊተ ብሩር፡

ዐሥሩን መክሊት ብር ተቀበል፤

ወጸውዮ ኪያሁኒ ውስተ በዓል፤

እርሱንም ወደ ሠርጉ ና በለው፡

፫፡ እስመ አምሐለኒ ራጉኤል ከመ ኢይፃዕ ዘእንበለ ይኅልፍ በዓል፤

በዓሉ ሳይፈጸም እንዳልወጣ ራጉኤል አምሎኛልና፤

፬፡ ወአቡየሰ ይኄልቍ መዋዕለ፤

አባቴ ግን ቀኑን ይቈጥራል፤

ወለእመ ጐንደይኩ ጥቀ የኀዝን፤

የዘገየሁም እንደሆነ እጅግ ያዝናል፡

፭፡ ወሖረ ሩፋኤል ወበጽሐ በኀበ ገባ ኤል፤

ሩፋኤልም ሄዶ ከገባኤል ዘንድ ደረሰ፤

ወመጠዎ መጽሐፈ፤

ደብዳቤውን ሰጠው፤

ወገባኤልኒ አምጽአ ዘኮ መስነቀ በማኅተም፤

ገባኤልም አቅማዳውን እንደ ተቋጠረ አምጥቶ፤

ወወሀቦ ለሩፋኤል፤

ለሩፋኤል ሰጠው፡

፮፡ ወጌሡ በጽባሕ ኀቡረ፤ ሲነጋ አንድ ሁነው ገሰገሡ፤

ወበጽሑ ውስተ በዓል፤

ከሠርጉ ደረሱ፤

ወባረከ ጦቢያ ሶበ አምጽአ ሎቱ ውእቱ ብሩረ፤

ጦቢያም ብሩን ባመጣለት ጊዜ መረቀው።

## ምዕራፍ ፲

፩፡ ወጦቢትሰ አቡሁ ለጦቢያ ይኄልቍ መዋዕለ፤

የጦቢያ አባት ጦቢት ግን ቀኑን ይቈጥር ነበረ፤

ወሶበ ተፈጸመ መዋዕለ ዕድሜሆሙ፤

የተቃጠሩበት ቀን በተፈጸመ ጊዜ፤

ወኢመጽኡ፤

እንደቀሩ ባየ ጊዜ፤

፪፡ ይቤ የጊ ተኃፍሩኑ ወልድየ፤

ልጄ የሚሰጠው አጥቶ አፍሮ ይሆንን፤

አው ይመውት ገባኤል፤

ወይስ ገባኤል ሙቶ ይሆን? አንድም ተኃለፈኑ ይላል፤ ልጄ ሙቶ ይሆን፤

ወኢረከበ ዘይሁቦ ብሩረ

ብሩን የሚሰጠው አላገኘ ይሆን? ብሎ፤

፫፡ ወተከዘ ጥቀ

እጅግ አዘነ።

፬፡ ወትቤሎ ብእሲቱ

ሚስቱ እንዲህ አለችው።

ወልድየሰ ሞተ ወበእንተዝ ጐንደየ

ልጄስ ሙቷል ስለዚህ ቀረ አለችው።

ወአኃዘት ትብክዮ

ታለቅስለት ጀመረች።

፭፡ ወትቤ እምኢየኅዘንኩ ወልድየ ሶበ አኮ ዘአኅጐልኩከ ብርሃነ አዕይንትየ

ወልድየ፤ ብርሃን አዕይንትየ ሲል ነው፤ ልጄስ ደኅና ከሆነ የብሩስ ጥፋት ባላሳዘነኝም ነበረ አለች።

፮፡ ወይቤላ አርምሚ

ዝም በይ አላት።

ወኢትትኃለፊ

እልፍ እልፍ ብለሽ አትናገሪ፤ አንድም ወኢትትኃለፊ ይላል፤ አትዘኝ አላት።

ውእቱሰ ሕያው

እሱስ ደኅና ነው።

፯፡ ወትቤሎ ይእቲኒ አርምም አንተኒ

እሷም አንተም ዝም በል አለችው።

ወኢታስተአብደኒ

አለአዋቂ አታድርገኝ።

ወልድየሰ ሞተ

ልጄስ ሙቷል።

ወተሐውር ኵሎ አሚረ ትብክዮ ውስተ ፍኖት እንተ ኀበ ሖረ።

ታለቅስለት ዘንድ ወደሄደበት ጐዳና ሁል ጊዜ ትሄድ ነበረ።

መዓልተ እክለ ኢትበልዕ

ቀን እህል አትቀምስም ነበረ።

ወሌሊተ ኢታረምም እንዘ ትበክዮ ለጦቢያ ወልዳ

ለልጇ ለጦብያ ስታለቅስ ሌሊትም ዝም አትልም ነበረ።

ወእስከ ተፈጸመ ዓሠርቱ ወረቡዕ ዕለት መዋዕለ በዓል

በዓል የሚደረግባቸው ዐሥራ አራቱ ቀን እስኪፈጸም ድረስ።

ዘአምሐሎ ራጉኤል ከመ ኢይሑር እስከ አመ ይትፌጸም በዓል ዘመርዓ

ሠርግ የሚደረግበት ቀን እስኪ ፈጸም ድረስ እንዳይሄድ ራጉኤል ያማለው።

፰፡ ወእምዝ ተፈጸሙ መዋዕለ በዓል

በዓል የሚደረግበት ቀን ከተፈ ጸመ በኋላ።

ይቤሎ ጦቢያ ለራጉኤል ፈንወኒ እንከሰ፡

ጦቢያ ራጉኤልን ከእንግዲህ ወዲህስ ስደደኝ አለው፤

እስመ አቡየ ወእምየ ቀብፁኒ፣

እናት አባቴ ተስፋ ቆርጠ ውብኛልና፤

ወኢይሴፈዉ እንከ ይርአዩኒ፣

ያዩኝ ዘንድ ተስፋ አያደር ጉምና፤

፱፡ ወይቤሎ ሐሙሁ ንበር ኀቤየ፣

አማቱ ራጉኤል ከኔ ጋራ ተቀመጥ አለው፤

ወአነ እልእክ ኀበ አቡከ ከመ ይንግርዎ ዜናከ፣

ደኅንነትህን ይነግሩት ዘንድ ወደ አባትህ እልካለሁ፤

፲፡ ወይቤሎ ጦቢያ አልቦ ጻዕሙ ፈንወኒ ኀበ አቡየ፣

ጦቢያም ወደአባቴ ስደደኝ እንጂ አይሆንም አለው፤

፲፩፡ ወተንሥአ ራጉኤል ወወሀበ ሣራሃ ብእሲቶ፣

ራጉኤልም ተነሥቶ ሚስቱን ሣራን ሰጠው፤

ወመንፈቀ ንዋዮሙ፣

የገንዘባቸውን እኩሌታ፤

ሰብአኒ ወእንስሳሁኒ፣

ሰውንም ከብቱንም ሰጠው፤

፲፪፡ ወባረኮሙ ወይቤሎሙ፣

መረቃቸው እንዲህ አላቸው፤

እግዚአ ሰማይ ያሠኒ ሳዕሌክሙ ደቂቅየ ዘእንበለ እሙት፣

ልጆቼ ሳልሞት ሰማይን የፈጠረ ጌታ በጎ ነገር ያድርግላችሁ፤

ወይቤላ ለወለቱ አክብሪ ታሕማኪ፣

ከእንግዲህ ወዲህስ አማትሽን አክብሪ፤

እስመ እሙይእዜ ዘመድኪ፤

ከዛሬ ጀምሮ ዘመድሽ እሱ ነውና፣

ወንሕነሰ ንስማዕ ዜና ሠናየ በላዕሌኪ፣

እኛም ባንቺ ላይ በጎ ወሬ እንሰማ ማለት ልጅ ወለደች ሲሉን እንሰማ፤

ወሰዓማ፣

ተሰናበታት፤

ወትቤሎ እድና ለጦቢያ

እድና ጦቢያን እንዲህ አለችው፤

አንተ እኁየ ዘአፈቅሮ እግዚአ ሰማይ ይሠርሕከ፣

አንተ ወንድሜ የምወደው ሰማይን የፈጠረ ጌታ ጉዳናውን ያቅናልህ፤

ወየሀብከ ወልደ እምነ ሣራ ወለትየ እርአይ ለከ፤

ከልጄ ከሣራ ወንድ ልጅ ተወልዶ አይ ዘንድ ልጅ ይስጥህ፤

ከመ እትፌሣሕ በቅድመ እግዚአ ብሔር፣

በእግዚአብሔር ዘንድ ደስ ይለኝ ዘንድ፤

ወናሁ አማኅፀንኩከ ወለትየ ማኅፀንተ ኢታኅዝና፣

እነሆ ልጄን አደራ ሰጥቼሃለሁ እንዳታሳዝናት በሷ ላይ ሌላ አታግባ፤

፲፫፡ ወእምድኅረዝ ሖረ ጦቢያ

ከዚህ በኋላ ጦብያ ወደሀገሩ ሄደ፣

ወባረኮ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን አመሰገነው፤

እስመ ሠርሐ ፍኖቶ፣

ጐዳናውን አቅንቶለታልና፤

ወባረኮሙ ራጉኤል ወእድና ብእሲቱ፣

ራጉኤልና እድናም አመሰገኑት፤

ወሖሩ ወቀርቡ ኀበ ነነዌ፣

ሄደው ወደነነዌ ቀረቡ።

## ምዕራፍ ፲፩

፩፡ ወእምዝ ይቤሎ ሩፋኤል ለጦቢያ፣

ከዚህ በኋላ ሩፋኤል ጦብያን እንዲህ አለው፤

አንተ እኁየ ኢተአምርኑ እፎ ኀደጋሁ ለአቡከ፣

አንተ ወንድሜ አባትህን በዕውርነት በንዴት እንደተውኸው አታውቅምን፤

፪፡ ነዓ ንቅድም እምነ ብእሲትከ፣

ከሚስትህ አስቀድመን ና እንሂድ፣

ወናስተዳሉ ቤተ

ቤቱን እናዘጋጅ፤

፫፡ ወንሣእ ምስሌከ ሐሞቶ ለዐሣ፣

የዚህን የአሣውን ሐሞት ያዝ አለው፤

ወሖሩ ክልኤሆሙ፣

ሁለቱም ሄዱ፤

ወሖረ ምስሌሆሙ ገኩ ወልድ ዘተለዎሙ፣

የተከተላቸው ያም ልጅ ከነዚያ ጋራ አብሯቸው ሄደ፤

፬፡ ወሐናሰ ትነብር ውስተ ፍኖት፣

ሐና ግን በጐዳና ተቀምጣ፤

ወትጸንሕ ምጽአቶ ለወልዳ፣

የልጇን መምጣት ትጠብቅ ነበረ፤

፭፡ ወርእየቶ እንዘ ይመጽእ፤

ሲመጣ አይታ፣

ሖረት ወነገረቶ ለአቡሁ፣

ሔዳ ላባቱ ነገረችው፤

ወትቤሎ ናሁ መጽአ ወልድከ፣

እነሆ ልጅህ መጣ አለችው፤

ወውእቱኒ ብእሲ ዘሖረ ምስሌሁ ውእቱኒ መጽአ፣

ከሱ ጋራ የሄደ ያም ሰው እሱም መጣ አለችው፤

፯፤ ወይቤሎ ሩፋኤል ለጦቢያ፣

ሩፋኤል ጦቢያን እንዲህ አለው፤

አነ አአምር ከመይትከሥት አዕይንቲሁ ለአቡከ፣

እኔም ያባትህ አይኖች እንዲገለጡ አውቃለሁ፤

፰፤ አንተሰ ኩሕሎ ዘንተ ሐሞተ አዕይንቲሁ፣

አንተ ግን ይህንን ሐሞቱን ዓይኑን ኳለው፤

ወሶበ ተኰሕለ የሐሲ፣

በተኳለ ጊዜ ያሸዋል፤

ወይወጽእ ዝኩ ጢስ እምኔሁ፣

ብልዙ፣ ብግሩ ከዓይኑ ይቀረፋል፣ ይገፈፋል፤

ወይሬኢ ጸጎኀ፣.

ድኖ ያያል፤

፱፤ ወሮፀት ሐና ወሐቀፈት ክሣደ ወልዳ፣

ሐና ፈጥና ሂዳ የልጇን አንገት አቀፈችው፤

ወትቤሎ እሙ እምይእዜሰ እሙት እንከ፣

እናቱ እንግዲህ ወዲህስ ልሙት አለችው፤

እስመ ርኢኩከ ወልድየ፣

ልጄ አይቼሃለሁና፤

ወበከዩ ክልኤሆሙ፣

ሁለቱም አለቀሱ፤

፲፤ ወወጽአ ጦቢት ኀበ ኖኀት፤

ጦቢት ወደ ደጅ ወጣ፤

ወተሐቅፉ፣

አንገት ለአንገት ተያያዙ፤ አንድም ወተአቅፈ ይላል ተሰነካከሉ ወደቀ፤

ወሮፀ ወልዱ ወአንሥአ ለአቡሁ፤

ልጁ ፈጥኖ ሂዶ አንገቱን ቀና አድርጎ፣

ወኰሐሎ ዝኩ ሐሞተ ውስተ አዕይንቲሁ፤

ይህን ሐሞቱን ዓይኑን ኳለው፤

፲፩፤ ወይቤሎ ተአመን አባ ከመ ተሐዩ፣

አባቴ እንድትድን እመን አለው፤

፲፪፤ ወሶበ ኰሐሎ ሐሰየ አዕይንቲሁ፣

በኳለው ጊዜ ዓይኑን አሸ፤

፲፪፡ ወተሠዐየ እምነ ብንተ አዕይንቲሁ፤

ከዓይኑ ብልዙ ብግሩ፤ ተቀረፈ፤ ተገፈፈ።

ወርእዮ ለወልዱ፤

ልጁን አየው።

፲፫፡ ወሐቀፎ ክሣዶ ወበከየ

አንገቱን አቅፎ አለቀሰ።

ወይቤ ቡሩክ አንተ እግዚኦ፤

አቤቱ አንተ ክቡር ምስጉን ነህ።

ወይትባረክ ስምከ ለዓለም፤

ስምህ ለዘለዓለም ይክበር ይመስገን።

ወቡሩካን ኵሎሙ መላእክቲከ ቅዱሳን፤

ቅዱሳን መላእክትህም ቡሩካን ናቸው።

፲፬፡ እስመ ቀሠፍከኒ፤

ከዚህ አስቀድሞ በመከራ ገርፈኸናልና።

ወተሣሃልከኒ፤

ተመልሰህ ይቅር ብለኸናልና። ስምህ ይክበር ይመስገን።

ወናሁ ርኢክዎ ለጦብያ ወልድየ፤

እነሆ ልጄ ጦብያን አየሁት።

ወእምዝ ቦአ ወልዱ እንዘ ይትፌሣሕ፤

ከዚህ በኋላ ልጁ ደስ ብሎት ገባ።

ወአይድዖ ለአቡሁ ኵሎ ዓቢያተ ዘኮነ ላዕሌሁ፤

በሚዲን ለሱ የተደረገውን ብዙውን ነገር ላባቱ ነገረው።

፲፭፡ ወወጽአ ጦቢት ወተቀበላ ለመርዓቱ እንዘ ይትፌሣሕ፤

ጦቢት ደስ ብሎት ምራቱን ተቀበላት።

ወባረከ ለእግዚአብሔር በኀበ አንቀጸ ነነዌ፤

በነነዌ አደባባይ እግዚአብሔርን አመሰገነው።

ወአንከሩ እለ ርእይዎ እንዘ የሐውር፤

ሲሄድ ያዩት ሰዎች ሁሉ አደነቁ።

ወይቤሉ እፎ ርእየ፤

እንደምን አየ አሉ።

፲፮፡ ወጦቢትሰ ገነየ ለእግዚአብሔር በቅድሜሆሙ።

ጦቢት ግን በፊታቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ።

እስመ ተሣሃሎ አምላከ ሰማይ፤

ሰማይን የፈጠረ እግዚአብሔር ይቅር ብሎታልና።

ወሶበ በጽሐ ጦቢት ኀበ ሣራ መርዓቱ፤

ጦቢት ከምራቱ ከሣራ በደረሰ ጊዜ።

ባረካ ወይቤላ በጸሐኪኑ በዳኅን ወለትየ፤

ልጄ በደኅና ደረስሽ አላት?።

ይትባረክ እግዚአብሔር ዘአምጽአኪ ኀቤነ፣

ወደኛ ያመጣሽ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፤

ወይባርክ አባኪኒ ወእመኪኒ

አባትሽንም እናትሽንም ያክብራቸው፤

ወኮነ ዓቢይ ትፍሥሕት ላዕለ ኵሉ አዝማዲሁ እለ ይነብሩ ነነዌ፣

በነነዌ በሚኖሩ በዘመዶች ሁሉ ብዙ ተድላ ደስታ ሆነ፤

፲፯፤ ወመጽአ አካኪሮስ ወነሳቦስ ወልደ እኁሁ፤

የወንድሙ ልጅ አካኪሮስና ነሳቦስ መጡ፤

፲፰፤ ወገብሩ በዓለ ሰቡዓ መዋዕለ በት ፍሥሕት፤

ሰባት ቀን በተድላ በደስታ በዓል አደረጉ፡፡

# ምዕራፍ ፲፪

## ጉባዔ

፩፤ ወእምዝ ጸውዖ ለጦቢያ ጦቢት፤

ከዚህ በኋላ ጦቢት ጦብያን ጠራው፣

ወይቤሎ ርኢ ለሉቱ ወልድየ አስበ ለዝኩ ብእሲ ዘሖረ ምስሌከ፤

ካንተ ጋራ የሄደውን የዚያን ሰው ደመወዙን ልጄ እይለት አለው፤ አንድም እወቅለት አለው፤

ወዓዲ ርቱዕ ትወስክ ሎቱ፣

ጸግመኛም ልትጨምርለት ይገባል፤

፪፤ ወይቤሎ ጦብያ ለአቡሁ አባ ዘይነክየኒ አልቦ ለእመ ወሀብክዎ መንፈቀ ዝንቱ ንዋይ ዘአምጻእኩ፣

ጦብያ አባቱን እንዲህ አለው፤ አባቴ ያመጣሁት የገንዘቡን እኩሌታ ብሰጠው የሚጎዳኝ የለም፤

፫፤ እስመ አዕተወኒ ኀቤከ በዳኅና፣

ወዳንተ በደህና መልሶኛልና፤

ወለብእሲትየኒ ፈወሳ፣

ሚስቴንም አድኗታልና፤

ወብሩረኒ አምጽአ፣

ብሩንም አምጥቷልና፤

ከማሁ ለከሂ ፈወሰከ፣

አሁንም እንደተናገርሁ አንተንም አድኖሃልና፤

፬፤ ወይቤሎ አቡሁ ጽድቀ ነበብከ፣

አባቱም እውነት ነገርን ተናገርህ አለው፤

፭፤ ወጸውዖ ለውእቱ መልአክ ወይቤሎ፤

መልአኩን ጠርቶ እንዲህ አለው፤

ንሣእ መንፈቀ ኵሉ ንዋይ ዘአምጻእከሙ ምስሌከሙ፣

ካንተ ጋራ ካመጣችሁት ገንዘብ እኩሌታውን ተቀበለህ፤

ወሑር በዳኅን፤

በደኅና ሂድ፤

፮፤ ወጸውዖሙ ሩፋኤል ውእተ ጊዜ ለክልኤሆሙ፣

ያን ጊዜ ሩፋኤል ሁለቱንም ጠራቸው፤

ወአግኃሦሙ ወይቤሎሙ፣

ከሰው ለይቶ እንዲህ አላቸው፤

ባርክዎ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርን አመስግኑት፤

ወግነዩ ሎቱ፤

ለሱ ተገዙት፤

ወወሀቡ ዕበየ ለስሙ፣

ስሙን አክብሩት፣ አግኑት፤

ወእመኑ ቦቱ በቅድመ ኵሉ ዘሕያው፣

በሕይወት በሚኖር ሰው ሁሉ ፊት እመኑበት፤

በእንተ ኵሉ ዘገብረ ላዕሌክሙ ሠናያተ፣

በናንተ ላይ ስላደረገው ስለ በጎ ነገሩ ሁሉ፤

ወአዕኵትዎ ለእግዚአብሔር፣

እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ን ም አመስ ግኑት፤

ወሰብሑ ለስሙ፣

ለስሙም ምስጋና አቅርቡ፤

ወንግሩ ግብሮ ለእግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔርን ሥራውን ተናገሩ፤

በክብር አርእዩ፣

ሥራውን አክብራችሁ ግለጹ፤

ወኢትትሐከዩ ገንየ ሎቱ፣

ለሱ መገዛቱን ቸል አትበሉ፤

፯፤ እስመ ምሥጢረ መንግሥት ሠናይ ለኀቢእ፣

የቤተ መንግሥትን ነገር ሊሰውሩት ይገባልና፤

ወለግብረ እግዚአብሔርሰ ይከሥትዎ በግብር፤

የእግዚአብሔር ታምራቱን ግን አክብሮ ሊገልጹት ይገባልና አክብራችሁ ግለጹት፤ አንድም ሠውሩት ያለውን ሊሠውሩት ግለጹት ያለውን ሊገልጹት ይገባልና፤

ግበርዋ ለሠናይት፣

በጎ ሥራን ሥሩት፤

ወኢትረክበክሙ እኪት፣

መከራ አታገኛችሁም፤

፰፤ ሠናይ ውእቱ ጸሎት ምስለ ሰላም፣

ጸሎት ከፍቅር ጋራ ያማረ ነው፤

ወምጽዋት፣

ከምጽዋት ጋራ ደግ ነው፤ አንድም ምጽዋት ደግ ናት፣

ወጽድቅ፣

ምግባርም ደግ ናት፤

ይኄይስ ኅዳጥ ዘበጽድቅ እምብዙኅ ብዕለ ዓመፃ፣

ሰርቆ ቀምቶ ካጠራቀሙት ከብዙ ገንዘብ በእውነት ሠርቶ ያጠራቀሙት ጥቂት ገንዘብ ይበልጣል፤ አንድም በማይገባ ሁኖ ብዙ ከመመጽወት በሚገባ ሁኖ ጥቂት መመጽወት ይሻላል፤

ወይኄይስ ውኂበ ምጽዋት እምዘጊቦቱ ለወርቅ፣

ወርቅ ከመሰብሰብ ምጽዋት መስጠት ይሻላል፤

፱፤ እስመ ምጽዋት ታድኅን እሞት፣

ምጽዋት ከሞተ ሥጋ፣ ከሞተ ነፍስ ታድናለችና፤

ወታነጽሕ እምኵሉ ኃጢአት፣

ከኃጢአት ሁሉ ታነፃለችና፣

ወእለሰ ይገብሩ ጽድቀ ወምጽዋተ ይመልኡ ላዕሌሆሙ ሕይወተ፣

በጎ ሥራ የሚሠሩ ምጽዋት የሚመጸውቱ ሰዎች ሕይወተ ሥጋን፤ አንድም ሕይወተ ነፍስን ያገኛሉ፤ አንድም ሕይወት ቢል በላያቸው በሰውነታቸው ሕይወት ይመላል፤

፲፤ ወእለሂ ይኤብሱ ይጸልእዋ ለነፍሶሙ፤

የሚበድሉም ሰዎች ሰውነታቸውን ይጠሏታል፤

፲፩፤ ወናሁ ኢየኀብእ እምኔክሙ ኵሎ ነገረ፤

ነገርን ሁሉ ከናንተ አልሰውርም፤

ወእቤለክሙ ከመ ምሥጢረ መንግሥት ሠናይ ለኃቢዕ፤

የቤተ መንግሥትን ነገር መሠወር እንዲገባ እነግራችኋለሁ፤

ወግብሮሰ ለእግዚአብሔር ይከሥትዎ በክብር፣

የእግዚአብሔርን ተአምራት ግን አክብሮ ሊገልጡት ይገባል፤

፲፪፤ ወይእዜኒ አመ ጸለይክሙ አንተ ወሣራ መርዓትከ፣

ሚስትህ ሣራና አንተ ጸሎት በጸለያችሁ ጊዜ፤

አነ አባዕኩ ተዝካረ ስእለትክሙ ቅድሜሁ ለቅዱሰ ቅዱሳን፣

እኔ የልመናችሁን መታሰቢያ መላእክት ወደሚያመሰግኑት ወደጌታ ፊት አቀረብሁላችሁ፤

ወአንተኒ አመ ትቀብር አብድንተ፣

አንተም ሬሳ በምትቀብርበት ጊዜ፤

አሜሃ ሀሎኩ ምስሌከ፣

ያን ጊዜ አብሬህ ነበርሁ፤

፲፫፤ ወአመኒ ኢተሐየይከ ወተንሣእከ ኅዲገከ ምስሐከ፣

ምሳህን ትተህ ቸል ሳትል በተነሣህ ጊዜ፤

ወሖርከ ትቅብር በድነ፣

ሬሳውን ልትቀብር በሄድህ ጊዜ፤

ወኢረሣእከ ገቢረ ሠናይ፣

በጎ ነገርን መሥራት ባሰብህ ጊዜ፤

አሜሃ ሀሎኩ ምስሌከ፣

ያን ጊዜ ካንተ ጋራ ነበርሁ፣ ይህ የኋላ ግብሩ ነው፤

፲፬፤ ወእግዚአብሔር ፈነወኒ ከመ እፈውስከ፤

አድንህ ዘንድ እግዚአብሔር የሰደደኝ፤

ወለሣራ መርዓትከ ከመ እናገዝዝ ኃዘና፣

ምራትህ ሣራንም ኃዘኗን አስተዋት ዘንድ የላከኝ፤

፲፭፤ አነ ውእቱ ሩፋኤል መልአክ አሐዱ እምነ ሰብአቱ ሊቃነ መላእክት ቅዱሳን እለ የዓርጉ ጸሎቶሙ ለቅዱሳን፣

የቅዱሳንን ጸሎት ከሚያሳርጉ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ እኔ ሩፋኤል ነኝ፤

ወያበውዑ ቅድመ ስብሐቲሁ ለዓቢይ ወቅዱስ፣

ጽኑ ገናና ወደሚሆን ወደጌት ነቱ ፊት ከሚያቀርቡ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ እኔ ነኝ፤

፲፮፤ ወሰሚያሙ ዘንተ ደንገፁ ክልኤሆሙ ወወድቁ በገጾሙ፤

ሁለቱም ይህንን በሰሙ ጊዜ ደንግጠው በግምባራቸው ፍግግም ብለው ወደቁ፤

እስመ ፈርሁ፤

ፈርተዋልና፤

፲፯፤ ወይቤሎሙ ኢትፍርሁ ለእግዚ አብሔር አምላክክሙ ባርክዎ፣

ፈጣሪያችሁን እግዚአብሔርን አመስግኑት እንጂ አትፍሩ፤

፲፰፤ እስመ አኮ ሊተ አኩቴት፣

እኔን ልታመሰግኑኝ አይገባ ምና፤

አላ ፈቃዱ ለአምላክክሙ አምጽአኒ፣

የፈጣሪያችሁ ፈቃዱ አመጣኝ እንጂ፤

ወበእንተዝ ባርክዎ ለአምላክ ጽድቅ ለዓለም፣

ስለዚህ ነገር የባሕርይ አምላክ የሚሆን እሱን ለዘለዓለም አመስግኑት፤

፲፱፤ ወበኵሉ መዋዕል፤

ባለበዘመናችሁ ሁሉ አመስግ ኑት፤

ወአነ አስተርአይኩክሙ፤

እኔም ታየኋችሁ ተነጋገር ኋችሁ፣

ወርኢክሙ ራእይየ፣

መልኬንም አያችሁ፤

ኢበላዕኩ ወኢሰተይኩ ምስሌክሙ፣

ከናንተ ጋራ ይረባኛል ይጠቅ መኛል ብዬ አልበላሁም አልጠ ጣሁም፤ አንድም ብደክም ያጸናኛል ተርቤ ያጠግበኛል ብዬ የበላሁ አይደለም፤

፳፡ ወይእዜኒ እመኑ በእግዚአብሔር፡

አሁንም በእግዚአብሔር እመኑ፤

እስመ ዓርግ ኀበ ዘፈነወኒ፣

ወደላከኝ ወደ እግዚአብሔር እሄዳለሁና፤

ወመጽእከ እጽሐፍ እሉንተ መጻሕፍተ፣

እነዚህን መጻሕፍት ልጽፍ መጣሁ፤ ወመጽአ ይጽሐፍም ይላል፤

፳፩፡ ወሶቤሃ ተንሥአ ወሐረ፣

ያን ጊዜ ተነሥቶ ሄደ፤

ወኢርእይዎ እንከ፣

ከዚያ በኋላ አላዩትም፤

፳፪፡ ወአምኑ በኵሉ ግብሩ ለእግዚአብሔር ዓቢይ ወግሩም፡

ገናና ድንቅ የሚሆን የእግዚአብሔርን ሥራውን አመኑ፤

ወበእንተ ዘአስተርአዮሙ መልአከ እግዚአብሔር፤

መልአከ እግዚአብሔር ስለታያቸውም አመኑ።

## ምዕራፍ ፲፫

፩፡ ወጸለየ ጦቢት ጸሎተ ትፍሥሕት፡

ተናገረ ሲል ነው፤ ጦቢት ደስ የሚያሰኝ ነገር ተናገረ፤ ጸሎት ብሂል ተናግሮተ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር እንዲል፣ አንድም ወጸሐፈ ጦቢት ይላል፤

ወይቤ ይትባረክ እግዚአብሔር ዘውእቱ ሕያው ዘለዓለም፤

ለዘለዓለም ሕያው የሚሆን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፤

ወለዓለመ ዓለም መንግሥቱ፣

መንግሥቱ ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፡

፪፡ ወውእቱ ይቀሥፍ ወይሣሃል፡

እሱ በመከራ ይገርፋል፣ ይቅር ይላል፣ ይቀሥፍ፣ ጠላቱን፣ ወይሣሃል ወዳጁን፤ አንድም ይቀሥፍ በሥጋ ወይሣሃል በነፍስ፣ በሥጋ ይቀሥፋል፣ በነፍስ ያድናል፤

ወውእቱ ያወርድ ውስተ ሲኦል ወየዐርግ፣

ወደመቃብር ያወርዳል፣ ከመቃብር ያስነሣል ፤ አንዱንም አንዱን ማናቸውን፤ አንድም አልዓዛርን፤ አንድም ጠላቱን ወደመቃበር ያወርዳል፤ ወዳጁንም ከመቃብር ያወጣል፤ አንድም ያወርድ በሥጋ፤ ወየዓርግ በነፍስ ያድናል፤

ወአልቦ ዘያመስጥ እምእዴሁ፤

ከሥልጣኑ የሚያመልጥ የለም፤

፫፣ ወግነዩ ሎቱ ኵልክሙ ደቂቀ እስራኤል፣

የእስራኤል ልጆች ሁላችሁ ተገዙለት፤

በቅድመ ኵሉ አሕዛብ እለ ዘረወነ ውስቴቶሙ፣

አስማርኮ ወደርሳቸው በሰደደን በአሕዛብ ፊት ተገዙለት፤

፬፤ በህየ አርአየ ምሕረቶ ላዕሌነ፣

በዚያ ይቅርታውን ገለጸልን፤

ወአልዕልዎ በቅድመ ኵሉ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው፣

በሰው ሁሉ ፊት እግዚአብሔርን አክብሩት አግኑት፤

እስመ ውእቱ እግዚእነ፣

ጌታችን እሱ ነውና፤

ወውእቱ እግዚአብሔር አቡነ በኵሉ ዓለም፤

በዓለሙ ሁሉ አባታችን እሱ ነውና፤

፭፤ ወይቀሥፈነ በኵሉ ኃጣውኢነ፣

በኃጢአታችን ይፈርድብናል፤

ወካዕበ ይሣሃለነ፤

ዳግመኛ ይቅር ይለናል፣ የመከራውን ለደስታ፤ አንድም የአባቶቻችውን ደስታ ለነሱ ካዕበ አለው፤

ወያስተጋብአነ እምኵሉ አሕዛብ እለ ውስቴቶሙ ዘረወነ፣

አስማርኮ ከበተነን ከአሕዛብ ሀገር ሁሉ ይሰበስበናል፤

፮፤ ወለእመኒ ተመየጥነ ኀቤሁ በኵሉ ልብነ፣

በፍጹም ልቡናችን ወደሱ ብንመለስ፤

ወበኵሉ ነፍስነ

በፍጹም ሰውነታችን ብንመለስ፤

ከመ ንግበር ጽድቀ በቅድሜሁ፣

በፊቱ በጎ ሥራ እንሠራ ዘንድ፤

ወውእተ ጊዜ ይትመየጥ ኀቤነ፣

ያን ጊዜ ከመዓት ወደምሕረት ይመለሳልና፤

ወኢይሜውር ገጸ እምኔነ፣

ገጸ ረድኤቱን ከኛ አልመለሰም፤

ወርእዩ ዘገብረ በላዕሌነ፣

ለኛ ያደረገውን አስተውሉ፤

ወእመኑ ቦቱ በኵሉ ልብክሙ፣

በፍጹም ልቡናችሁ እመኑበት፤

ወበኵሉ ነፍስክሙ፣

በፍጹም ሰውነታችሁ እመኑበት፤

ወባርክዎ ለእግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን አመስግኑት፤

ወአልዕልዎ ለንጉሠ ዓለም በምድር ዘተፄወውክሙ፣

ተማርካችሁ በሄዳችሁበት ሀገር የዓለሙ ሁሉ ንጉሥ የሚሆን እሱን አመስግኑት፤

ወአንሰ በምድር ዘተፄወውኩ አአምን ቦቱ፣

እኔም ተማርኬ በሄድሁበት ሀገር አምንበታለሁ፤

ወእነግር ኃይሎ ወዕበዮ ለሕዝብ ኃጥአን፣

ለኃጥአን ወገኖች ከሀሊነቱን፣ ገናንነቱን እናገራለሁ፤

ተመየጡ ኃጥአን ወግበርዋ ለጽድቅ ቅድሜሁ ለእግዚእየ፣

ኃጥአን ከክፋት ወደበጎነት ተመለሱ፤ በጌታዬ ፊት በጎ ሥራን ሥሩት፤

መኑ የአምሮ እመ ይፈቅድ ዘይገብር ምሕረቶ በላዕሌክሙ አምላኪየ፣

ፈጣሪዬ፤ ይቅርታውን በናንተ ላይ ያደርግ ዘንድ እንዲወድ ማን ያውቃል፣ እሱን መጠ ራጠር አይደለም፣ የነሱን አለመመለስ መናገር ነው፤

፯፤ ወታሌዕሎ ነፍስየ ለንጉሠ ሰማይ፤

የሰማይ ንጉሥ የሚሆን እሱን ሰውነቴ ከፍ ከፍ ታደርገ ዋለች።

እሴብሖ ዕበዮ ለአምላከ ጽድቅ በኵሉ፤

የባሕርይ አምላክ የሚሆን እሱን ገናንነቱን በውስጥ በአፍአ አመሰግነዋለሁ፤

፰፤ ወእመኒ ቦቱ በጽድቅ ሀገረ ኢየሩሳሌም ቅድስት፣

ክብርት የምትሆኝ ኢየሩሳ ሌም በእውነት እመኝበት፣

ኢይቅሥፍኪኑ በምግባረ ጽድቅኪ፤

በምግባርሽ ዳኚ እንጂ በመከራ አልግረፍሽን፤ አንድም ኢይቀ ሠፊኪኑ በምግባረ ደቂቅኪ፣ በልጆችሽ ኃጢአት በመከራ አልገርፍሽምን፤

ወካዕበ ይምሕከሙ ለደቂቀ ጻድቃን፣

ዳግመኛም የጻድቃንን ልጆች ያዝንላቸዋል፤

፱፤ ግነዩ ለእግዚአብሔር በሠናይ፣

በጐ ሥራ በመሥራት ለእግዚ አብሔር ተገዙ፣

ወባርኪዮ ለንጉሠ ዓለም ከመ ትትሐነፅ ደብተራሁ ውስቴትኪ በትፍሥሕት፣

ቤተ መቅደስ በተድላ በደስታ ትሠራ ዘንድ የዓለሙ ሁሉ ንጉሥ የሚሆን እሱን አመስ ግኘው፤

ወይትፌሣሑ ብኪ ህየ እለ ሀለዉ ፂውዋን፣

ተማርከው በዚያ የሚኖሩ ሁሉ ባንቺ ደስ ይላቸዋል፤

ወይትፌቀሩ በእንቲአኪ ጽሉዓን በኵሉ ትውልድ ዘለዓለም፤

የተጠሉ ሰዎች ባንቺ ምክንያት ለዘለዓለም በሚኖር ትውልድ ደስ ይላቸዋል፤

፲፩፤ እስመ ብዙኃን አሕዛብ ይመጽኡ እምርኁቅ ኀበ ስሙ ለእግዚአ ብሔር፤

ብዙ አሕዛብ በእግዚአብሔር ስም አምነው ከሩቅ ይመጣሉና፤

ወያመጽኡ አምኃ ለንጉሠ ዓለም ወለንጉሠ ሰማይ፤

ለዓለም ንጉሥና ለሰማይ ንጉሥ ለእግዚአብሔር እጅ መንሻ ያመጣሉ፤

ለትውልደ ትውልድ ይሴብሑከ እግዚኦ፤

አቤቱ ለልጅ ልጅ ዘመን ያመሰ ግኑሃል፤

ወይሁቡ ስብሐተ ለስምከ፤

ለስምህ ምስጋና ያቀርቡ ዘንድ፤

፲፬፤ ርጉማን ኵሎሙ እለ ይጸልኡከ፤

አንተን የሚጠሉህ ሰዎች ርጉማን ናቸው፤

ወቡሩካን እሙንቱ ኵሎሙ እለ ያፈቅሩከ ለዓለም፤

ለዘለዓሙ አንተን የሚያመ ሰግኑህ ሁሉ ክቡራን ልዑላን ናቸው፤

፲፪፤ ወትትፌሣሕ በደቂቆሙ ለጻድቃን፤

በጻድቃን ልጆች ደስ ይልሃል፤

እስመ ይትጋብኡ ወይባርኩከ እግዚኦ፤

አቤቱ ተሰብስበው ያመሰግኑ ሃልና፤

እስመ ብፁዓን እሙንቱ እለ ያፈቅሩከ፤

የሚወዱህ ሰዎች ክቡራን ንዑ ዳን ናቸውና፤

ወይትፌሥሑ በስምከ፤

በስምህ አምነው ደስ ይላቸዋል፤

፲፫፤ ወብፁዓን ኵሎሙ እለ ይቴክዙ በሕማምከ፤

ባመጣህባቸው መከራ የሚያ ዝኑ ሰዎች ልዑላን ንዑዳን ናቸው፤

እስመ ይትፌሥሑ ብከ ርእዮሙ ኵሎ ስብሐቲከ፤

ጌትነትህን፣ ተአምራትህን አይ ተው ደስ ይላቸዋልና፤ አንድም በዕለተ ዓርብ በተቀበልከው መከራ የሚያዝኑ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው፤ ጸጋህን ክብር ህን አይተው ደስ ይላቸዋልና፤

ወይትፌሥሑ ለዓለም፤

ለዘለዓለም ደስ ይላቸዋልና፤

፲፭፤ ነፍስነሰ ትባርኮ ለእግዚአብሔር ንጉሠ ዓቢይ፣

ገናና ንጉሥ የሚሆን እግዚአብሔርን ሰውነታችን ታመስግነዋለች፤

፲፮፤ እስመ ትትሐነፅ ኢየሩሳሌም በዕብነ ሰንፔር ወበመረግድ ወበዕንቍ ክቡር፣

ኢየሩሳሌም ሰንፔር መረግድ በሚባል በከበረ ዕንቍ ትሠራለችና፤

አረፋቲሃ፣

ድልድሏ፤

ወማሕፈዲሃ፣

ግንቧ፤

ወአናቅጺሃ፣

በሯ፤

በወርቅ ንጹሕ፣

በጠራ ወርቅ ትሠራለች፤

፲፯፤ ወመርኅባኒ፣

አደባባይዋ፤

በቢረሌ፣

ብርሌ በሚባል ዕንቍ፤

ወበዕንቈ ሶፎር አትራኮስ፣

አትራኮስ በሚባል ዕንቍ፤

ወበዕንቈ ሶፎር ይትገበር፣

ሶፎር በሚባል ዕንቍ ይሠራል፤

፲፰፤ ወይብሉ በኵሉ ፍናዊሃ ሃሌ ሉያ

በአራት ማዕዘኗ ስብሐት ለእግዚአብሔር እያሉ ያመሰግናሉ፤ አንድም እስመ ትትሐ ነፅ ኢየሩሳሌም በሰንፔር ወመረግድ፣ ወበዕንቍ ክቡር ቤተ ክርስቲያን በሦስት ስም ትጸናለችና፤ አረፋቲሃኒ ሰውነቷ ወማኅፈዲሃኒ፣ ሕዋሳቷ ወአናቅጺሃ፣ ልቡናዋ በወርቅ ንጹሕ በሕገ ወንጌል ይጸናል፤ ወመርኅባኒ፤ በቢረሌ ወበዕንቈ፤ አትራኮስ ወበዕንቈ ሶፎር ይትገበር፣ ልቡናዋ በሦስቱ ስም ይጸናል፤ ወይብሉ በኵሉ ፍናዊሃ፣ ሃሌ ሉያ በአደባባይዋ ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘሀሎ ወይሄሉ እያሉ ያመሰግናሉ፤

ይሴብሑ ወይብሉ ይትባረክ እግዚአብሔር ለዓለም፣

እግዚአብሔር ለዘለዓለሙ ይክበር ይመስገን እያሉ ያመሰግናሉ፤

ወበኵሉ ዓለም፣

በአራቱ ማእዘን ምስጋና ይገባል እያሉ።።

## ምዕራፍ ፲፬

፩፤ ወእምዝ አርመመ ጦቢት እምነበ ይጼሊ፣

ከዚህ በኋላ ጦቢት ጸሎቱን ተወ፣

፪፤ ኃምሳ ወሰመንቱ ዓመት ሎቱ አመ የኃጕል አዕይንቲሁ፤

ጦቢት ዓይኑ በጠፋ ጊዜ ኃምሳ ስምንት ዘመን ሆኖት ነበር፤

ወእምድኅረ ኃምሳ ወሰመንቱ ዓመት ርእየ፤

ከኃምሳ ስምንት ዘመን በኋላ አየ፤

ወገብረ ምጽዋተ፣

ምጽዋት መጸወተ፤

ወወሰከ ዓዲ ፈሪሆቶ ለእግዚአ ብሔር፤

ደግመኛም እግዚአብሔርን እጅግ ፈራው፤

፫፤ ወፈድፋደ ረስዓ፣

ፈጽሞ አረጀ፤

ወጸውዖሙ ለወልዱ ወለደቂቀ ወልዱ፣

ልጁን፣ የልጅ ልጁን ጠርቶ፤

ወይቤሎ ወልድየ ንሣእ ደቂቀከ፣

ልጄ ልጆችህን ውሰድ፤

እስመ ረሣዕኩ ወበጻሕኩ እስከ ለሞት፣

ለሞት እስከደርስ ድረስ አርጅ ቻለሁና፤

፬፤ ወሑር እስከ ሜዶን፣

ወደሚዶን ሂድ አለው፤

እስመ አእምር ኵሎ ዘነበበ ዮናስ ነቢይ ላዕለ ነነዌ ከመ ሀለዋ ትትነሠት፣

ትጠፋ ዘንድ እንዳላት ዮናስ በነነዌ የተናገረውን አውቃ ለሁና፤

ውስተ ሜዶንሰ ሰላም ይከውን፣ እስከ ዘመኑ፣

በሜዶን ግን እስከ ጊዜው ድረስ ተድላ ደስታ ይሆናል፤ አንድም እስከ ዘመዱ ይላል፤ እስከ ዳርዮስ ድረስ፤

ወአኃዊነ ሀለዎሙ ይዘረዉ ውስተ በሐውርት እምነ ኵሉ ምድር ቡርክት፣

ክብርት ቡርክት ከሆነች ከኢየ ሩሳሌም ተማርከው በየሀገሩ ይበተኑ ዘንድ አላቸው፤

ወኢየሩሳሌምኒ ትከውን በድወ፣

ኢየሩሳሌም ምድረበዳ ትሆና ለች፤

ወቤተ እግዚአብሔር ዘውስቴታ ይውዒ በእሳት፤

በውስጧ ያለ ቤተ መቅደስም በእሳት ይቃጠላል፣ የተቃጠ ለበት አልታወቀም፤

ወይከውን በድወ፣

እስከ ዘመኑ እስከ ጊዜው ድረስ ምድረበዳ ይሆናል፤ አንድም እስከ ዘመዱ እስከ ዘሩባቤል ድረስ፤

፭፤ ወካዕበ ይሣሀሎሙ እግዚአ ብሔር ወያገብኦሙ ውስተ ምድሮሙ፣

ደግመኛ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸዋል ወደ ሀገራቸው ይመልሳቸዋል፤

ወየሐንፁ ቤቶ፤

ቤተ መቅደስን ይሠራሉ፤

ወአኮ ከመ ቀዲሙ፤

እንቀደመው የሚፈርስ አይደለም፤

አላ እስከ ይትፌጸም መዋዕለ ዓለም፤

ዓለም እስኪያልፍ ድረስ ይኖራል እንጂ፤

ወእምድኅረ ዝንቱ ይገብኡ እምነበ ይጼወዉ፤

ከዚህ በኋላ ከተማረኩበት ይመለሳሉ፤

ወይትሐነፅ ኢየሩሳሌም በክብር ፤

ኢየሩሳሌምን በክብር አክብረው ይሠሯታል፤

ወይትሐነፅ በውስቴታ ቤተ እግዚአብሔር በኵሉ ትውልድ ዘለዓለም፤

በውስጧም ለልጅ ልጅ የሚሆን ቤተ እግዚአብሔር ለዘለዓለም ይሠራል፤

በንድቅ ክቡር፤

በዕብነ ሩካም ይሠራል፤

፮፤ ወኵሉ አሕዛብ ይገድፉ አማልክቲሆሙ፤

አሕዛብ ሁሉ ጣዖቱን ይጥላሉ፤

ወይትመየጡ በጽድቅ፤

በእውነት ይመለሳሉ፤

፯፤ ወይፈርህዎ ለእግዚአብሔር ወይባርክዎ፤

እግዚአብሔርን ፈርተው ያመሰግኑታል፤

ወሕዝብኒ የአምኑ ቦቱ፤

ሕዝቡም ያምኑበታል፤

ወይሣሀሎሙ እግዚአብሔር ለሕዝቡ፤

እግዚአብሔር ወገኖቹን ይቅር ይላቸዋል፤

ወይትፌሥሑ ኵሎሙ እለ ይፈርህዎ ለእግዚአብሔር በጽድቅ ወበርትዕ፤

በእውነት ነገር በቀና ነገር ጸንተው እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ሰዎች ደስ ይላቸዋል፤

ወይገብሩ ምሕረተ ላዕለ አኃዊሆሙ፤

ወንድሞቻቸውን ይቅር ይሏቸዋል፤

፰፤ ወይእዜኒ ወልድየ ፃዕ እምነነዌ፤

አሁንም ልጄ ከነነዌ ውጣ፤

እስመ በግብር ይከውን ዘነበበ ዮናስ ነቢይ፤

ነቢዩ ዮናስ የተናገረው ነገር ግድ ይደረጋልና፤

፱፤ ወአንተሰ ዕቀብ ሕገ ወትእዛዘ፤

አንተ ግን ሕጉን ትእዛዙን ጠብቅ፤

ወኩን መሐሬ፣

ለሰው የምታዝን ሁን፤

ወአፍቅር ጽድቀ ከመ ይኩን ሠናየ ላዕሌከ፤

ላንተ በጎ ነገር ይሆንልህ ዘንድ ምጽዋትን ውደድ፤

፲፤ ወቅብረኒ በሠናይ፣

አክብረህ ቅበረኝ፤

ወለእምከኒ ምስሌየ፣

እናትህንም ከኔ ጋራ ደርባት፤

ወኢትንበር ውስተ ነነዌ ወልድየ፣

ልጄ በነነዌ አትቀመጥ፤

ወርኢ ዘከመ ገብረ ሐማ ላዕለ አካኪሮስ፤

ሐማ በዘመድህ በአካኪሮስ ላይ ያደረገውን አስተውል፤ ያልታ ወቀ ነው፤ አንድም ሐማ በመ ርዶክዮስ ያደረገውን እወቅ፤

ወከመ አብአ እምብርሃን ውስተ ጽልመት፣

ከተድላ ከደስታ ወደመከራ እንዳገባው እወቅ፤

ወእመ ተፈድየ በከመ አከዩ፣

እንደክፋቱ ፍዳውን እንደ ተቀበለ፤

ወአካኪሮንስ ሕያው ውእቱ፣

አካኪሮስ ግን ከመከራ ዳነ፤

አንድም መርዶክዮስ ከመከ ራው ዳነ፤

ወውእቱሰ ተፈድየ ፍዳሁ፣

ሐማ ግን ፍዳውን ተቀበለ፤

ወለሊሁ ወረደ ውስተ ጽልመት፣

እሱ ወደመቃብር፤ አንድም ወደሲኦል ወረደ፤

ወምናሴ ገብረ ምጽዋተ፣

ምናሴም ምጽዋት ሰጠ፤

ወገብረ ጽድቀ፣

በጎ ሥራ ሠራ

ወድኅነ እምነ መቅሠፍተ ሞት እንተ ሠርዑ ላዕሌሁ፣

በእሱ ላይ ካዘዙበት ሞትን ከሚያስከትል መቅሠፍት ዳነ፤

ወሐማሰ ወድቀ ውስተ ይእቲ መሥገርት፤

ሐማ ግን በመከረው ምክር ጠፋ፤

ወሞተ፣ ሞተ፣

ሞትን ሞተ፣

፲፩፤ ወይእዜኒ ርኢ ወልድየ ከመ ታድኅን ምጽዋት ለእለ ይገብርዋ፤

ልጄ ምጽዋት ለሚያደርጓት ሰዎች እንድታድን እወቅ፤

ወትፌሪ ጽድቀ፣

ዋጋ እንድታሰጥ እወቅ፤

ወከመዝ ብሂሎ ሞተ ጠቢት፣

ይህንን ተናግሮ ጠቢት ሞተ፤

ወወጽአት መንፈሱ በጺበ ዓራቱ፣

ባልጋው ላይ ሳለ ነፍሱ ከሥጋው ተለየች፤

ምዕት ወኃምሣ ወሰመንቱ ዓመት ሎቱ፤

በሞተ ጊዜ መቶ ኃምሳ ስምንት ዘመን ሆኖት ነበር፤

ወቀበርዎ በክብር፣

አክብረው ቀበሩት፤

፲፪፡ ወአመ ሞተት ሐና እሙ ቀበራ ጦቢያ ወልዱ ምስለ አቡሁ፣

ሐናም በሞተች ጊዜ ልጁ ጦብያ ከአባቱ ደረባት፤

ወሖረ ጦብያ ምስለ ብእሲቱ ወደቂቁ ውስተ ባጥና ኀበ ራጉኤል፣

ጦብያ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋራ ወደ ራጉኤል ዘንድ ወደባጥና ሄደ፤

፲፫፡ ወረስዐ ራጉኤል ወእድና ብእሲቱ፣

ራጉኤል አረጀ፤ እድና ሚስቱም አረጀች፤

ወሞቱ፣

ሞቱ፤

ወቀበሮሙ ጦብያ በክብር ለኃሕማሁ፤

ጦብያ አማቶቹን አክብሮ ቀበራቸው፤

ወተዋረሰሙ ኵሎ ንዋዮሙ፣

ገንዘባቸውንም ወረሰ፤

ወለጦቢትኒ አቡሁ፣

አባቱ ጦቢትንም ወረሰ፤

፲፬፡ ወሰምዐ ጦብያ ሙስናሃ ለነነዌ ዘእንበለ ይሙት በከመ ነገሮ አቡሁ፤

አባቱ እንደተናገረው ሳይሞት ጦብያ የነነዌን ጥፋት ሰማ፤

ወሰምዑ ናቡከደነፆር ወአሕሻዊሮስ ሙስናሃ ለነነዌ ወተፈሥሑ፤

ናቡከደነፆርና አሕሻዊሮስ የነነዌን ጥፋት ሰምተው ደስ አላቸው፤ እሊህማ አጥፊዎች አይደሉም ምነው ሰሙ አለ ቢሉ ሥራዊቶቻቸውን ሰደው አስወግተዋቸው ነበርና ከሥራ ዊቶቻቸው የነነዌን ጥፋት ሰሙ አለ፤

፲፭፡ ወሞተ ጦብያ በ፻ወ፳ወ፯ቱ ዓመት በባጥና ዘሜዶን፣

ጦብያ የሜዶን አውራጃ በምትሆን በባጥና በመቶ ኻያ ሰባት ዓመት ሞተ፤

ወቀበርዎ በክብር፣

አክብረው ቀበሩት፤

ተፈጸመ መጽሐፈ ጦቢት በረከተ አምላኩ ትኩን ምስሌነ፤ ወስብሐት ለእግዚአብሔር እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን።

የጦቢት ጉባዔ ፬ ነው።